የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ

ቁጥር 23/2014

ሰኔ/ 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

መግቢያ

የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ሥራ ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ፍትሐዊ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ እና ተደራሽ በማድረግ የንግዱን ማኅበረሰብ እና ኅብረተሰቡ ከንግዱ ሥርዓት የሚጠብቀውን አገልግሎት እንዲያገኝ የሕግና የአሠራር ክፍተቶችን በመድፈንና እርካታን በማሳደግ በአገሪቱ ሁለንተናዊ ኢኮኖሚ ውስጥ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ማድረግ በማስፈለጉ፤

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ ወጭን የሚቀንስና ቀልጣፋ የአገልግሎት መስጫ በቀጥታ መስመር በመዘርጋት የንግድ ሥራ አመቺነትን ለማዳበር፣ እንዲሁም የንግድ ሥርዓቱ ለመረጃ አያያዝ አመቺ እንዲሆን፣ሕገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴን ለመግታት የሚያስችል እና ለኅብረተሰቡ እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የንግድ ስርዓቱ ፍትሐዊ የንግድ ውድድርን እንዲከተል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ እና በድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ሥራዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ተመሳሳይ አፈጻጸምን ማስፈን እንዲቻል በማስፈለጉ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በንግድ ሕጉ የመግቢያ ድንጋጌ አንቀጽ 5 መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና የድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 23/2014” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጉም

በዚህ መመሪያ

1. “**የንግድ ሕግ**” ማለት የኢፊዴሪ የንግድ ሕግ 1243/2013 ነው፤
2. “**አዋጅ**” ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 /እንደተሻሻለ/ (1150/2011) ማለት ነው፤
3. “**ደንብ**” ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 392/2009 /እንደተሻሻለ/ (461/2012) ማለት ነው፤

4. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተደነገጉት የቃላት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በነጋዴዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 (በአዋጅ ቁጥር 1150/2011 እንደተሻሻለ) የተፈጻሚነት ወሰን ለዚህም የሚያገለግል ሆኖ በንግድ ሕጉ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይም ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት
የድርጅት ስም እና የንግድ ስም ስለመመዝገብ፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ

4. የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ድርጅት ስም ስለመመዝገብ

ማንኛውም የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ድርጅት ስም ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ያቀርባል፣
2. በአዋጁ ድንጋጌ መሠረት የንግድ ድርጅት ስሙን ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ በማጣራት ይመዘገባል።

5. የንግድ ማኅበር የንግድ ድርጅት ስም ስለመመዝገብ

ማንኛውም የንግድ ማኅበር የንግድ ድርጅት ስም ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ቢያንስ ሦስት አማራጭ የንግድ ድርጅት ስሞችን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. የንግድ ማኅበር የንግድ ድርጅት ስም ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ በማጣራት ይመዘገባል፤
3. ተጣርቶ የተመዘገበውን የንግድ ድርጅት ስም የማኅበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ እንዲጸድቅ፤የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲያገኙ ሰነድን ለማረጋገጥ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለመስጠት በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በደብዳቤ ይሸኛል፤ ወይም በደብዳቤ መሸኘት ሳያስፈልግ በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ይደረጋል፤
4. ተጣርቶ የተሰጠው የንግድ ድርጅት ስም ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፀድቆ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ወጥቶለት

ለመዝጋቢው አካል ቀርቦ በንግድ ምዝገባ መመዝገብ አለበት፤

5. የተጣራው የንግድ ድርጅት ስም የማይመዘገብ ሆኖ ከተገኘ መዝጋቢው አካል የማይመዘግብበትን ምክንያት ገልፆ አመልካቹ ከጠየቀ ወዲያውኑ በጽሑፍ ያሳውቃል፤

6. የሽርክና ማኅበራት የአባላቱን ስም ወይም ቢያንስ የሁለት አባላቱን ስም ወይንም ከአባላቱ ሥሞች በምህጻረ ቃል የተውጣጣ በድርጅት ስምነት የሚጠቀም ሲሆን የአክሲዮን ማኅበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፣ እና ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የፈጠራ ስም መጠቀም አለባቸው፤

7. በአዋጁ በተደነገገው መሠረት የሚደረግ የንግድ ድርጅት ስም ምዝገባ የንግድ ምዝገባ በሚያደርግበት ቦታ መመዝገብ አለበት።

8. በተራ ቁጥር 7 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በንግድ ስም መመሪያ ተመዝግቦ የተሰጡ የድርጅት ስሞች የንግድ ምዝገባ ከሚያደርጉበት ቦታ ምዝገባቸውን መውሰድ ይችላሉ።

9. በአደራጆች በመቋቋም ላይ ያለ አክሲን ማኅበር የንግድ ምዝገባ ማመልከቻ በአደራጆች ሰብሳቢ ወይም በሥራ አስኪያጁ የሚቀርብ ሆኖ፣ አክሲዮን ማኅበሩ በንግድ መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት፣ አደራጆች ለአደራጅነት ብቁ ስለመሆናቸው ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የድጋፍ ደብዳቤ ምዝገባውን ለሚያከናውነው አካል ማቅረብ አለባቸው።

10. መዝጋቢው አካል የምዝገባ ማመልከቻው እንደቀረበለት ረቂቅ የድርጅት ስሞችን፣ የንግድ ዓላማውን፣ የአክሲዮን መጠን፣ አድራሻ፣ ምዝገባ የሚከናወንበትን ቦታ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ማጣራቶችን አድርጎ ስሙን በጊዜያዊነት ካጸደቀ በኋላ፣ አደራጆቹ አክሲዮን ማኅበር ለማደራጅት ብቁ ስለመሆናቸው የድጋፍ ደብዳቤ እንዲያቀርቡ፣ በጊዜያዊነት የጸደቀውን ስሙን፣ የንግድ ዓላማውን፣ እና የሁሉንም አደራጆች መሉ ስም ከነአድራሻቸው በመጥቀስ ወደንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት ይልካቸዋል።

11. የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 249 መሠረት አመልካቾች ለአደራጅነት ብቁ መሆናቸውን አጣርቶ፣ አመልካቾች የጠየቁትን የንግድ ምዝገባ ለሚያከናውነው አካል በጊዜያዊነት የጸደቀውን ስሙን፣ የንግድ ዓላማውን፣ የሁሉንም አደራጆች መሉ ስም ከነአድራሻቸው እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በመጥቀስ የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል።

12. አደራጆች ተገቢውን የድጋፍ ደብዳቤ ለመዝጋቢው አካል እንዳቀረቡ፣ መዝጋቢው አካል የሥራ

አስኪያጁን ወይም የአደራጆችን ሰብሳቢ መሉ ስም፣ የታደሰ መታወቂያ እና የፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶ ግራፍ እና ሌሎች ሰነዶችን እንዲያሟላ በማድረግ የአክሲዮን ማኅበሩን ስም በቋሚነት ካጸደቀ በኋላ፣ የአክሲዮን ሽያጭ ገንዘብ ገቢ የሚደረግበት ዝግ የባንክ ሒሳብ በሚቋቋመው የአክሲዮን ማኅበር ስም እንዲከፈት ለባንኮች፣ እንዲሁም የማኅበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ እንዲጸድቅ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲያገኝ ሰነድን ለማረጋገጥ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለመስጠት በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በደብዳቤ ይሸኛል፤ ወይም በደብዳቤ መሸኘት ሳያስፈልግ በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ይደረጋል።

13. የአክሲዮን ሽያጭ ገንዘብ ገቢ የሚደረገው በሚቋቋመው የአክሲዮን ማኅበር ስም በሚከፈቱ ዝግ የባንክ ሒሳቦች ብቻ ይሆናል። እነኝህ በሚቋቋመው የአክሲዮን ማኅበር ስም የሚከፈቱ ዝግ የባንክ ሒሳቦች ሊንቀሳቀሱ የሚችሉት ማኅበሩ የምሥረታ ኦዲትን ጨምሮ ሁሉንም የምሥረታ ሂደት ጨርሶና ማኅበሩን ለባለአክሲዮኖቹ ካስረከበ በኋላ ከሚመለከተው አካል ሒሳቦቹን ማንቀሳቀስ ይቻላል የሚል ፈቃድ ሲሰጥ ብቻ ነው።

14. አደራጆች ለሥራ ማስጂያጃ የሚጠቀሙበት የባንክ ሒሳብ በስማቸው መክፈት ይችላሉ።

6. የንግድ ማኅበር የንግድ ድርጅት ስም ስለመለወጥ

ማንኛውም የንግድ ማኅበር የንግድ ድርጅት ስም ለመለወጥ፤አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ቢያንስ ሦስት አማራጭ የንግድ ድርጅት ስሞችን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. የንግድ ማኅበራት የንግድ ድርጅት ስምን ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ በማጣራት ይመዘገባል፤
3. ለመለወጥ፤ የተዘጋጀው ያልጸደቀ ቃለ ጉባኤ ለመዝጋቢው አካል እንዲቀርብ ተደርጎ በማጣራት እንዲጸድቅ ሰነድን ለማረጋገጥ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲያሻሽል በሕግ ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት በደብዳቤ ይሸኛል ወይም በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም አገልግሎቱ እንዲሰጥ ይደረጋል፤
4. ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ ቃለ ጉባኤ እና የድርጅቱ ስም ተለውጦ፤እንዲመዘገብ ከግብር አስከፋዩ መስሪያ ቤት የስምምነት ደብዳቤ ይዞ ሲቀርብ የተለወጠው፤ የድርጅት ስም ይመዘገባል፤

5. የተለወጠው የንግድ ድርጅት ስም ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፀድቆ ለመዝጋቢው ቀርቦ ካልተመዘገበ የቀድሞው የንግድ ድርጅት ስም እንደተለወጠ አይቆጠርም።

7. የንግድ ስምን ስለመመዝገብ

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ቢያንስ ሦስት አማራጭ የንግድ ስሞችን ሞልቶ እንዲያቀርብ ይደረጋል፤
2. በደንቡ መስፈርት እና በዚህ መመሪያ መሠረት የንግድ ስሙ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ ይጣራል፤
3. የተጣራው የንግድ ስም በሌላ ነጋዴ አለመያዙ ከተረጋገጠ በኋላ በአባሪ II ቅጽ 03 የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
4. ተጣርቶ የተሰጠው የንግድ ስም በስህተት ወይም በሌላ ምክንያት ለሌላ ነጋዴ ተሰጥቶ ከተገኘ እና በመሰጠቱ ቅሬታ ከቀረበ የንግድ ስሙን ቅድሚያ የወሰደው ነጋዴ ባለመብት እንዲሆን ተደርጎ በኋላ የወሰደው ነጋዴ ሌላ የንግድ ስም ቀይሮ እንዲያወጣ ይደረጋል፤
5. በአዋጁ መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ በሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች በሚሰጥባቸው የንግድ ሥራ መደቦች ላይ የንግድ ስም ምዝገባ ሲጠየቅ አገልግሎቱን የሚያገኙት የንግድ ሥራ ፈቃድ መሰጠቱን አረጋግጦ የንግድ ምዝገባ ባደረጉበት ቦታ ይሆናል፤
6. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም በመታሰቢያነት እንዲመዘገብ ሲጠይቅ በመታሰቢያነት የሚጠቀምበት በወራሾች ስምምነትን ያገኘ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

8. የንግድ ስምን ስለመለወጥ፤

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም ምዝገባ ለመለወጥ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ቢያንስ ሦስት አማራጭ የንግድ ስሞችን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መስፈርት መሠረት የንግድ ስሙ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ ይጣራል፤

3. የተጣራው የንግድ ስም በሌላ ነጋዴ አለመያዙ ከተረጋገጠ በኋላ በአባሪ II ቅጽ 03 የተለወጠበት የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

4. ተጣርቶ የተሰጠው የንግድ ስም በስህተት ወይም በሌላ ምክንያት ለሌላ ነጋዴ ተሰጥቶ ከተገኘ እና በመሰጠቱ ቅሬታ ከቀረበ የንግድ ስሙን ቅድሚያ የወሰደው ነጋዴ ባለመብት እንዲሆን ተደርጎ በኋላ የወሰደው ነጋዴ ሌላ የንግድ ስም እንዲያወጣ ይደረጋል፤

5. የተለወጠው የንግድ ስም በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ በመጠቀም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድኅረ ገጽ የንግድ ስም እና አድራሻ ይፋ ይደረጋል።

9. ምትክ የንግድ ስም

ማንኛውም ነጋዴ ምትክ የንግድ ስም አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ምትክ የንግድ ስም እንዲሰጠው እንዲጠይቅ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መስፈርት እና በዚህ መመሪያ መሠረት የጠየቀው አገልግሎት በአባሪ II ቅጽ 03 ምትክ የንግድ ስም የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ይደረጋል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቶች በኦንላይን በሚሰጡበት ጊዜ ተገልጋዩ በቀጥታ ምትክ ማውጣት ይችላል።

10. የንግድ ስም ስረዛ

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪI ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ስም እንዲሰረዝለት እንዲጠይቅ ይደረጋል፤

2. የተጠየቀውን የንግድ ስም በመሰረዝ የስረዛ ማስረጃ ይሰጣል።

ክፍል ሦስት
የንግድ ምዝገባ ስለ መመዝገብ ስለ ማሻሻል፣ ስለ ምትክ እና ስለስረዛ

11. የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት

አገር አቀፍ ተፈፃሚነት ያለው የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በሥራ ቋንቋ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

12. የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ምዝገባ ስለመመዝገብ

ማንኛውም ግለሰብ ነጋዴየንግድ ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያአባሪ I ቅጽ02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ምዝገባ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. የጠየቀው አገልግሎት በደንቡ መሠረት መስፈርቶችን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01መሠረት የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
3. አካለ መጠን ባልደረሰ ሰው ሐብት ውስጥ እና በፍርድ የተከለከለ ሰው ሃብት ውስጥ የንግድ ድርጅት የተገኘ እንደሆነ ሞግዚቱ የንግድ ድርጅቱን ሥራ እንዲቀጥል በፍርድ ቤት የተወሰነበት ማስረጃ መቅረብ አለበት።
4. የግለሰብ ነጋዴ ካፒታል ለንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት አገልግሎት ለማግኘት በሞላው አባሪ I ቅጽ 02 ላይ የመዘገበው የገንዘብ መጠን ካፒታል ነው ተብሎ ይመዘገባል።

13. የንግድ ማኅበር የንግድ ምዝገባ ስለመመዝገብ

ማንኛውም የንግድ ማኅበር የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ምዝገባ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በንግድ ሕጉ ላይ የተቀመጠው ዝቅተኛ ዋና ገንዘብ መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ማኅበራት በመመሥረቻ/በመግለጫ ፅሁፎቻቸው ላይ የመዘገቡት የገንዘብ መጠን ካፒታል ነው ተብሎ ይመዘገባል፤ሆኖም የአክስዮን ማኅበር እና ኃላፊነታቸው ተወሰነ የግል ማኅበራት በንግድ ሕጉ የተቀመጠው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን እና በዝግ ሂሳብ የሚያሳዩት መጠን የተጠበቀ ነው።

3. በአዋጁ መሠረት የንግድ ማኅበር ስለመቋቋሙ በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድኅረ ገጽ የድርጅቱ ስም እና አድራሻ ይፋ ይደረጋል፤

4. አካለ መጠን ባልደረሰ ሰው ሐብት ውስጥ እና በፍርድ የተከለከለ ሰው ሃብት ውስጥ ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የንግድ ድርጅት የተገኘ እንደሆነ ሞግዚቱ የንግድ ድርጅቱን ሥራ እንዲቀጥል በፍርድ ቤት የተወሰነበት ማስረጃ መቅረብ አለበት።

5. የጠየቀው አገልግሎት በደንቡ መሠረት መስፈርቶችን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01 መሠረት የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

6. ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ሙያተኞች የሆኑ አባላቱ የሙያ ምስክር ወረቀት ለመስጠት በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የጸና የሙያ ማርጋገጫ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሌላ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ከሆነ ከሚመሠረተው ማኅበር ጋር ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ የሆነ የሙያ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የጸና የሙያ ፈቃድ ያለው መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

7. ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ማኅበሩን የሚመሰርትበት መግለጫ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ የንብረት ጠባቂነት ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት። በተጨማሪም የኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የተደነገጉ ድንጋጌዎች ለዚህም ያገለግላሉ።

8. የምዝገባ አገልግሎት የጠየቀው ለህዝብ ክፍት የሆነ የአክስዮን ማኅበር ከሆነ በውጭ ኦዲተር የተመረመረበትን የምሥረታ ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

14. የንግድ ምዝገባን ስለማሻሻል

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ምዝገባ ማሻሻል ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መስፈርት መሠረት የተጠየቀው የማሻሻያ አገልግሎት ሲፈቀድ አገልግሎቱ በበይነ መረብ /ኦንላይን/ በሚሰጥባቸው ቦታዎች ማሻሻያው ሲስተሙ ላይ እንዲታይ በማድረግ እንዲሁም ኦንላይን አገልግሎት ተደራሽ ባልሆነበት ቦታ ነጋዴው ቀድሞ የወሰደውን የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ እንዲመልስ በማድረግ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01 መሠረት የተሻሻለ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

3. የንግድ ማኅበር የካፒታል ማሻሻያ በሚያደርግበትና የካፒታል ማሻሻያው በጥሬ ገንዘብ በሚሆንበት

ጊዜ ገንዘቡ በአባላቱ የተመዘገበበት ሰነድ እና ሰነድን ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል በእያንዳንዳቸው ስም የተመዘገበ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፣

4. የንግድ ማኅበር የካፒታል ማሻሻያ በሚያደርግበትና የካፒታል ማሻሻያው በዓይነት በሚሆንበት ጊዜ በአባላቱ ሙሉ ድምፅ ስምምነት የተደረገበት ሰነድ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የፀደቀ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤

5. የንግድ ማኅበር የካፒታል ማሻሻያ በሚያደርግበትና የካፒታል ማሻሻያው ከትርፍ ክፍፍል የሚደረግ ከሆነ ማኅበሩ ያስመዘገበው ትርፍ ስለመኖሩ በኦዲት ሪፖርት ላይ ተረጋግጦ በአባላቱ ጠቅላላ ስምምነት የተደረገበት ሰነድ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤

6. በንግድ ሕጉ መሠረት የአክስዮን ማኅበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፣ እና ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የካፒታል ቅነሳ ለማድረግ ኦዲተሮች ዋና ገንዘቡን መቀነስ ያስፈለገበትን ምክንያት እና በአቀናነሱ ሁኔታ ላይ ለጠቅላላ ጉባኤው ማቅረባቸውን እና በጉባኤው የተወሰነበትን የሚያሳይ ማስረጃ በቃለ ጉባኤ ፀድቆ መቅረብ አለበት፤

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት የሚደረግ የካፒታል ቅነሳ ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ ወጥቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ ቅነሳው ይመዘገባል።

15. ምትክ የንግድ ምዝገባ ስለመስጠት

ማንኛውም ነጋዴ ምትክ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 02 በተዘጋጀውየማመልከቻ ቅጽ ላይ ምትክ የንግድ ምዝገባ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መስፈርት መሠረት የተጠየቀው ምትክ የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ሲፈቀድ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01 መሠረት ምትክ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቶች በኦንላይን በሚሰጡበት ጊዜ ተገልጋዩ በቀጥታ ምትክ ማውጣት ይችላል።

16. የንግድ ምዝገባ ስረዛ

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ምዝገባ ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 02 በተዘጋጀውየማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ምዝገባ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማኅበር የንግድ ምዝገባ ሲሰረዝ አባላቱ በሰየሙት ሒሣብ አጣሪና በደንቡ መስፈርት መሟላቱን በማረጋገጥ አገልግሎቱ በበይነ መረብ /ኦንላይን/ በሚሰጥባቸው ቦታዎች ስረዛው ሲስተሙ ላይ እንዲታይ በማድረግ እንዲሁም ኦንላይን አገልግሎት ተደራሽ ባልሆነበት ቦታ ነጋዴው ቀድሞ የወሰደውን የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ እንዲመልስ በማድረግ የንግድ ምዝገባ ስረዛ ደብዳቤ ይሰጣል፤

3. ማንኛውም የንግድ ምዝገባ ስረዛ ሲከናወን መዝጋቢው አካል ስረዛውን ለጠየቀው አካል በተሰየመው የሒሳብ አጣሪ በኩል በደብዳቤ ይገልፃል፤

4. በአዋጁ መሠረት የንግድ ማኅበራት ምዝገባ ስረዛ የሚጸናው የስረዛው ማስታወቂያ በአመልካቹ ወጪ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ከአንድ ወር በኋላ መሆኑ ተረጋግጦ አገልግሎቱ ይሰጣል፤

5. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ተፈጻሚነት ሲባል የበላይ ኃላፊ ማለት ከፌዴራል እስከ አካባቢ አስተዳደር ያሉ ንግድን የሚያስተዳድሩ አካላት ናቸው።

17. በማዕድን ዘርፍ የሚሰማራ የውጭ አገር ነጋዴ የንግድ ምዝገባ

በማዕድን ዘርፍ የተሰማራ የውጭ ሀገር ነጋዴ የንግድ ምዝገባን በተመለከተ በዓለም ዓቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነው ለሚገቡ የውጭ ሀገር ድርጅቶች የተቀመጠው መስፈርት (ከውል ስምምነት ሰነድ በስተቀር) የሚያገለግል ሆኖ በተጨማሪ ማዕድንን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የይመዝገብልኝ የድጋፍ ደብዳቤ ማምጣት አለበት።

ክፍል ዐራት
የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት፣ ስለማደስ፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ

18. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ሥራ ፈቃድ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የተጠየቀው የንግድ ሥራ ፈቃድ አገልግሎት ሲፈቀድ በዚህ መመሪያአባሪ II ቅጽ 02 መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

3. በዓለም ዓቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆኖ የሚገባ ነጋዴ በጨረታ አሸናፊ ከሆነበት የንግድ ሥራ በተጨማሪ ሌላ ጨረታ ያሸነፈ ከሆነ ላሸነፈበት ጨረታ ተጨማሪ የንግድ ሥራ ፈቃድ የማውጣት ግዴታ አለበት፤

4. በትራንስፖርት ዘርፍ ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ አገልግሎት ሲጠይቁ ለሌሎች ነጋዴዎች የተቀመጡት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በተጨማሪ የተሸከርካሪው የባለቤትነት ማረጋገጫ/ሊብሬ/ ተያይዞ መቅረብ አለበት።

19. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለማደስ

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማደስ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 03 በተዘጋጀውየማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲሰረጋገጥበዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 02 መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

3. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር 10 እና ከዚያ በላይ ባለ አክስዮኖች ያሉት እንደሆነ ወይም የማኅበሩ ጠቅላላ ሃብት ብር 10,000,000 ሚሊዮን /ዐሥር ሚሊዮን ብር/ በላይ ከሆነ ነጻና ገለልተኛ በሆነ የውጭ ኦዲተር የተሰራ የኦዲት ሪፖርት መቅረብ አለበት።

4. ኃላፊነቱ ያልተወሰነ የንግድ ማኅበር በዕድሣት ወቅት የኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርብ አይገደድም፣

5. ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማኅበር በእድሳት ወቅት የሚያቀርበው የኦዲት ሪፖርት ሁለት የበጀት ዓመት ያላለፈው መሆን አለበት፤

6. ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማኅበራት የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በ¾ኛ ከጎደለ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካለ ቦርዱ ወይም ሥራ አስኪያጆች የጎደለውን መዋጮ በባለአክስዮኖች እንዲተካ ማድረግ አለባቸው። ባለአክስዮኖች ማኅበሩ እንዲቀጥል በቃለ ጉባኤ የወሰኑ እንደሆነ ዋና ገንዘቡን ከ1/4ኛ በላይ እንዲሆን በማድረግ የማኅበሩን ፈቃድ ማሳደስ ይችላሉ። ሆኖም ዋና ገንዘቡ በ¾ኛ መጉደሉ ከታወቀ አስንቶ በ90 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ካልተፈጸመ ጥቅም ያለው ሰው ማኅበሩ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት የማፍረሻ ትዕዛዝ ለመዝጋቢው አካል በማቅረብ የንግድ ማኅበሩ እንዲሰረዝ ሊያደርግ ይችላል።

በዚህን ጊዜ ማኅበሩ ከሥረዛ በስተቀር ማንኛውንም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መጠየቅ አይችልም።

7. የአክስዮን ማኅበር የዋና ገንዘቡን ¾ኛ በኪሣራ ያጣ እንደሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ የማኅበሩን መፍረስ ወይም መቀጠል የሚወስን አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት አለበት። ባለአክስዮኖችም ማኅበሩ እንዲቀጥል በቃለ ጉባኤ የወሰኑ እንደሆነ ዋና ገንዘቡን ከ1/4ኛ በላይ እንዲሆን በማድረግ የማኅበሩን ፈቃድ ማሳደስ ይችላሉ።

8. የካፒታል ጭመራ ወይም ቅነሳ ያደረጉ ነጋዴዎች በንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀታቸው ላይ የተደረገውን ማሻሻያ/ለውጥ/ የንግድ ሥራ ፈቃዳቸውም ላይ ይመዘገባል።

9. አዲስ የሚቋቋም ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማኅበር እስከ ሁለት የበጀት አመት የኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርብ አይገደድም፤

10. ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማኅበር የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማሳደስ የንግድ ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይም ማኅበሩን ወክሎ በማኅበሩ ስም ይህንን ጉዳይ እንዲያስፈጽም ሕጋዊ ውክልና በተሰጠው ሰው መታደስ ይችላል፤

11. የመረጃ መረብ ባለበት ቦታ ሁሉ የቀረበው የግብር ክሊራንስ ትክክለኛ ስለመሆኑ ግብር ለመሰብሰብ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የመረጃ መረብ መረጋገጥ አለበት፤

12. ግብርን ለመሰብሰብ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ጋር የመረጃ መረብ ግንኙነት በሌለበት ቦታ የቀረበው የግብር ክሊራንስ ግብር ለመሰብሰብ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠው መረጃ ትክክለኛ ነው ተብሎ ይወሰዳል፤

13. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 እና 12 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረበው የግብር ክሊራንስ ትክክለኛ ስለመሆኑ አመቺ በሆነው መንገድ ሁሉ መዝጋቢው አካል ማረጋገጥ አለበት፤

14. ቀደም ሲል በየትኛውም የሥራ መደብ የንግድ ሥራ ፈቃድ አውጥቶ ሲሰራ ቆይቶ በማንኛውም ምክንያት የንግድ ሥራ ፈቃዱ የተሰረዘበት ወይም በቅጣት ላይ ያለ ነጋዴ አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሲያወጣ ቀድሞ ሲሰራበት ለነበረው የንግድ ሥራ ፈቃድ የግብር ክሊራንስ ማቅረብ አለበት፤

15. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚያስፈልጋቸውን የንግድ ሥራ ፈቃድ መደቦችን በተመለከተ በመመሪያ በተወሰነው/በሚወሰነው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

20. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለ ማሻሻል

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 03 በተዘጋጀውየማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ሥራ ፈቃድ የማሻሻል ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲሰረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 02 መሠረት የተሻሻለ የንግድ ሥራ ፈቃድየምስክር ወረቀትይሰጣል፡፡

3. የአገልግሎት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች ተሸከርካሪ ከሆነ ብዛቱ ከጨመረ ወይም ተሸከርካሪው በተለወጠ ጊዜ የቻንሲ እና የሰሌዳ ቁጥር በማስመዝገብ ወይም ሌላ የአገልግሎት ዘርፍ ከሆነ የተደረገውን ማሻሻያ ወይም ለውጥ በማስመዝገብ የንግድ ሥራ ፈቃዳቸው እንዲሻሻል ይደረጋል።

21. ስለ ምትክ የንግድ ሥራ ፈቃድ

ማንኛውም ነጋዴ ምትክ የንግድ ሥራ ፈቃድ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ምትክ የንግድ ሥራ ፈቃድ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ተረጋግጦ በዚህ መመሪያ አባሪ IIቅጽ 02 መሠረት ምትክ የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቶች በኦንላይን በሚሰጡበት ጊዜ ተገልጋዩ በቀጥታ ምትክ ማውጣት ይችላል።

22. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርቱ መሟላቱ ሲረጋገጥ አገልግሎቱ በበይነ መረብ /ኦንላይን/ በሚሰጥባቸው ቦታዎች የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛው ሲስተሙ ላይ እንዲታይ በማድረግ እንዲሁም ኦንላይን አገልግሎት ተደራሽ ባልሆነበት ቦታ ነጋዴው ቀድሞ የወሰደውን የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት

ዋና ቅጂ እንዲመልስ በማድረግ የተጠየቀው የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ ማስረጃ ደብዳቤ ይሰጣል፤

3. ማንኛውም የንግድ ሥራ ፈቃድ ሲሰረዝ ስረዛውን ለጠየቀው እና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል።

4. ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማኅበራት የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በ¾ኛ ከጎደለ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ካለ ቦርዱ ወይም ሥራ አስኪያጆች ዋና ገንዘቡን ከ1/4ኛ በላይ እንዲሆን ማድረግ ካልቻሉ ጥቅም ያለው ሰው ማኅበሩ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት የማፍረሻ ትዕዛዝ ለመዝጋቢው አካል በማቅረብ የንግድ ማኅበሩ እንዲሰረዝ ሊያደርግ ይችላል። በዚህን ጊዜ ማኅበሩ ከሥረዛ በስተቀር ማንኛውንም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መጠየቅ አይችልም።

5. የአክስዮን ማኅበር የዋና ገንዘቡን ¾ኛ በኪሣራ ያጣ እንደሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ የማኅበሩን መፍረስ ወይም መቀጠል የሚወስን አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት አለበት። ባለአክስዮኖችም ማኅበሩ እንዲቀጥል በቃለ ጉባኤ ወስነው ዋና ገንዘቡን ከ1/4ኛ በላይ እንዲሆን ማድረግ ካልቻሉ ጥቅም ያለው ሰው ማኅበሩ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት የማፍረሻ ትዕዛዝ ለመዝጋቢው አካል በማቅረብ የንግድ ማኅበሩ እንዲሰረዝ ሊያደርግ ይችላል።

ክፍል አምስት
በልዩ ምዝገባ ስለመመዝገብ፣ ስለዕድሳት፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ

23. የዘርፍ ማኅበራት፣ የውጭ ሀገር ንግድ ምክር ቤቶች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ምዝገባ፣ የሆልዲንግ /የቡድን/ ኩባንያ እና የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ

ማንኛውም አመልካች የዘርፍ ማኅበር፣ የውጭ ሀገር ንግድ ምክር ቤት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ምዝገባ፣ የሆልዲንግ ኩባንያ ወይም የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 04 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. የተጠየቀው አገልግሎት

   ሀ. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 06 መሠረት የዘርፍ ማኅበራት ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

   ለ. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 07 መሠረት የውጭ ሀገር ንግድ ምክር ቤቶች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

ሐ. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 08 መሠረት የሆልዲንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

መ. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 09 መሠረት የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀትይሰጣል።

24. የሆልዲንግ/የቡድን/ ኩባንያ እና የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ ዕድሳት

ማንኛውም አመልካች የሆልዲንግ ወይም የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ ዕድሳት አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 04 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የልዩ ምዝገባ ዕድሳት ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. የተጠየቀው አገልግሎት
   ሀ. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 08 መሠረት የሆልዲንግ ልዩ ምዝገባ ዕድሳት ይደረጋል፣
   ለ. በደንቡ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 09 መሠረት የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ዕድሳት ይደረጋል፤

3. በፍራንቻይዝ ውሉ መሠረት ፍራንቻይዘሩ ከሚያገኘው ገቢ ተገቢውን ግብር መክፈሉን ፍራንቻይዚው ከግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ማስረጃ ያቀርባል።

25. የሆልዲንግ /የቡድን/ ኩባንያ ልዩ ምዝገባን ስለማሻሻል

ማንኛውም አመልካች የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ ምዝገባ ምስክር ወረቀት የማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 04 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የልዩ ምዝገባ ማሻሻል ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ ቀድሞ የወሰደውን የልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በመመለስ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 08 መሠረት የተሻሻለ የሆልዲንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

26. የሆልዲንግ /የቡድን/ ኩባንያ እና የፍራንቻይዚንግ ምትክ የልዩ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ማንኛውም አመልካች የሆልዲንግ ኩባንያ ወይም የፍራንቻይዚንግ ምትክ የልዩ ምዝገባ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 04 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ምትክ የልዩ ምዝገባ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. የተጠየቀው አገልግሎት

ሀ. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 08 መሠረት ምትክ የሆልዲንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

ለ. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 09 መሠረት ምትክ የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቶች በኦንላይን በሚሰጡበት ጊዜ ተገልጋዩ በቀጥታ ምትክ ማውጣት ይችላል።

27. የሆልዲንግ /የቡድን/ ኩባንያ እና የፍራንቻይዚንግ የልዩ ምዝገባ ስረዛ

ማንኛውም አመልካች የሆልዲንግ ኩባንያ ወይም የፍራንቻይዚንግ የልዩ ምዝገባ ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 04 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የልዩ ምዝገባ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. ሆልዲንግ ኩባንያን በሚመለከት፣ የሥረዛ አገልግሎት በሚጠየቅበት ጊዜ የሁሉም ኩባንያዎች የግብር መዝጊያ ክሊራንስ ማቅረብ አለበት፤
3. ፍራንቻይዚንግን በሚመለከት፣ የሥረዛ አገልግሎት በሚጠየቅበት ጊዜ የፍሬንቻይዚው የገቢ ግብር ክሊራንስ መቅረብ አለበት፤
4. የተጠየቀው አገልግሎት

ሀ. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ መሠረት የሆልዲንግ ኩባንያ የልዩ ምዝገባ ስረዛ ደብዳቤ ይሰጣል፤

ለ. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ መሠረት የልዩ ምዝገባ ስረዛ ደብዳቤ ይሰጣል፤

5. ማንኛውም የሆልዲንግ ኩባንያ ወይም የፍራንቻይዚንግ የልዩ ምዝገባ ሲሰረዝ ስረዛውን ለጠየቀው እና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል።

28. የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ማንኛውም የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማግኘት አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 06 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 05 መሠረት የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

29. የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስለማደስ

ማንኛውም የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት የማደስ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪI ቅጽ 06 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት የማደስ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 05 መሠረት የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀትዕድሳት ይሰጣል፤

30. የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስለማሻሻል

ማንኛውም የንግድ እንደራሴ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት የማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 06 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ማሻሻል ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. የተጠየቀው የማሻሻያ አገልግሎት ሲፈቀድ ቀድሞ የወሰደውን የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት በመመለስ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 05 መሠረት የተሻሻለ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

31. ስለ ምትክ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት

ማንኛውም የንግድ እንደራሴ ምትክ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀትአገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያአባሪ I ቅጽ 06 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ምትክ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 05 መሠረት ምትክ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቶች በኦንላይን በሚሰጡበት ጊዜ ተገልጋዩ በቀጥታ ምትክ ማውጣት ይችላል።

32. የእንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስረዛ

ማንኛውም የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ06 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 05 መሠረት የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ ተመላሽ ተደርጎ ስረዛ ይደረጋል፤
3. ማንኛውም የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ሲሰረዝ ስረዛውን ለጠየቀው እና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል።

33. የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ሥራ እንዲሰራ የተፈቀደለት ነጋዴ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 07 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥበዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 10 መሠረት የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

34. የጠረፍ ንግድ ምዝገባ ስረዛ

ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀትስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 07 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የጠረፍ ንግድ ምዝገባ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ የተጠየቀው የጠረፍ ንግድ ምዝገባ ስረዛ ይደረጋል፤

3. ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ምዝገባ ሲሰረዝ ስረዛውን ለጠየቀው እና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል።

35. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት

ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲያወጣ የተፈቀደለት ነጋዴ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 08 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 11 መሠረት የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

36. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለማደስ

ማንኛውም ነጋዴ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ እድሳት አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 08 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ የማደስ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 11 መሠረት የጠረፍ ንግድ ልዩ ንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ዕድሳት አገልግሎት ይሰጣል፤

37. ስለ ምትክ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ

ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ምትክ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 08 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ምትክ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 11 መሠረት ምትክ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቶች በኦንላይን በሚሰጡበት ጊዜ ተገልጋዩ በቀጥታ ምትክ ማውጣት ይችላል።

38. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ

ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ ቅጽ 08 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይየጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. በደንቡ መሠረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ የተጠየቀው የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ ይደረጋል፤

3. ማንኛውምየጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሲሰረዝ ስረዛው ለጠየቀው እና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል።

ክፍል ስድስት
የንግድ መደብርን ስለማስተላለፍ፣ ስለንግድ ማኅበራት መዋሃድና መከፈል

39. የንግድ መደብርን/ድርጅትን ስለማስተላለፍ የሚጠየቁ መስፈርቶች

1. የንግድ መደብሩ/ድርጅቱ ሲተላለፍ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ ውል፤

2. የነባሩ ንግድ ሥራ ፈቃድ የግብር መዝጊያ ክሊራንስ መቅረብ አለበት፣

3. የቀድሞ ባለቤት በስሙ የነበረውን የንግድ ሥራ ፈቃድ ተመላሽ ማድረግ አለበት፣

4. የንግድ መደብሩ/ድርጅቱ የተላለፈ መሆኑ በአገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ከተነገረበት ከአንድ ወር በኋላ ማስረጃ በማቅረብ የተላለፈለት ግለሰብ በስሙ የንግድ ምዝገባና የንግድ ሥራ ፈቃድ ማውጣት አለበት። ሆኖም የንግድ መደብሩ የተላለፈለት ነጋዴ በተመሳሳይ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ከሆነ በቅርንጫፍነት ሊያስመዘግብ ይችላል፤ ነጋዴ ሆኖ በተመሳሳይ መስክ ላይ ያልተሰማራ ከሆነ በነበረው ምዝገባ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያወጣል።

5. የሚተላለፈው የንግድ መደብር የንግድ ማኅበር በሆነ ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተገለፀው በተጨማሪ ማኅበሩን ለማስተላለፍ አባላቱ በሙሉ ድምፅ የተስማሙበት ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤

6. የሚተላለፈው የንግድ መደብር ለንግድ ማኅበር ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ከተገለፀው በተጨማሪ የሚተላለፍለት የንግድ ማኅበር የመመሥረቻ ጽሑፍ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚተላለፍለት የንግድ ማኅበር አባላት በሙሉ ድምፅ የተደረገ ስምምነት የፀደቀ ቃለ ጉባዔ መቅረብ አለበት፤

7. የሚተላለፈው የንግድ መደብር ለውጭ ሀገር ዜጋ ከሆነ ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው አባል የሚገኝበት የንግድ ማኅበር ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማቅረብ አለበት፤

8. የተሰማራበት የሥራ መስክ ለውጭ አገር ባለሀብት የተፈቀደ መሆኑ ይረጋገጣል።

40. ስለ ንግድ ኩባንያዎች ውህደት፤

1. የንግድ ኩባንያዎች በሚዋሃዱበት ጊዜ ውህደቱ የንግድ ውድድርን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የሚታይ ከሆነ ከዚህ አካል የተሰጠ የውህደት ፈቃድ ማረጋገጫ እና በሚዋሃዱት ኩባንያዎች ሙሉ አባላት የተፈረመ እና ሰነዶችን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤

2. ውህደቱ የንግድ ውድድርን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የማይታይ ከሆነ በሚዋሀዱት የንግድ ኩባንያዎች ሙሉ አባላት ድምጽ የተስማሙበት እና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤

3. የሚዋሀዱ ማንኛውም የንግድ ኩባንያዎች በተናጠል የመዝጊያ የግብር ክሊራንስ ማቅረብ አለባቸው፣ሆኖም ሲዋሃዱ ዕዳን ለማጠቃለል የተስማሙ ከሆነ የስምምነቱ ማረጋገጫ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን የተረጋገጠ ማስረጃ መቅረብ አለበት፤

4. የሚዋሀዱ ማንኛውም የንግድ ኩባንያዎች ውህደቱ የሚጠቀምበት የድርጅትና የንግድ ስሞችን በመለየት ማቅረብ አለባቸው፤

5. የሚዋሀዱ ማንኛውም የንግድ ኩባንያዎች ከሚዋሀዱት ኩባንያዎች የድርጅት ስም እና የንግድ ስም ውጪ ሌላ አዲስ የድርጅት እና/ወይም የንግድ ስም የሚጠቀሙ ከሆነየነበራቸው የድርጅት እና የንግድ ስሞች እንዲሰረዙ ይደረጋሉ፤ አዲሱን ስም በቃለ ጉባዔ በማሻሻል ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል እንዲጸድቅ መደረግ አለበት፤

6. የንግድ ኩባንያዎች ከሚዋሃዱት የንግድ ኩባንያዎች የአንዱን የድርጅትና የንግድ ስም የሚጠቀሙ ከሆነ የተቀሩት የድርጅትና የንግድ ስሞች እንዲሰረዙ ይደረጋል።

41. ስለንግድ ኩባንያዎች መከፈል፤

1. የሚከፈል የንግድ ኩባንያ ከመከፈሉ በፊት የገቢ ክሊራንስ ማቅረብና የሂሳብ መዝገቡን ማዘጋት አለበት፤

2. የሚከፈለው የንግድ ድርጅት የተከፈለው አካል ከሌላ የንግድ ኩባንያ ጋር የሚዋሃድ ከሆነ በሚዋሃደው የንግድ ኩባንያ የድርጅት ስምና የንግድ ስም ይጠቃለላል፤

3. የሚከፈለው የንግድ ኩባንያ የተከፋፈሉ አካሎች ራሳቸውን ችለው የሚመሠረቱ ከሆነ ከመከፋፈሉ በፊት በነበረው የድርጅትና የንግድ ስም የሚጠቀምበት ክፋይ አካል የትኛው እንደሆነ ከመከፈሉ በፊት በነበሩት ሙሉ አባላት የተፈረመ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ-ጉባኤ መቅረብ አለበት፤

4. የተከፈሉት አካላት የአባላት ዝርዝር፣ ካፒታል፣ የድርጅት ስም፣ የንግድ ስም እና የመሳሰሉት ስለንግድ ኩባንያዎች በንግድ ሕጉ፣ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ደንብና መመሪያ የተደነገጉት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

ክፍል ሰባት
ስለንግድ ማኅበራት ሕጋዊ አቋም ለውጥ

42. የንግድ ማኅበር ሕጋዊ አቋም ስለመለወጥ፤

ማናቸውም የንግድ ማኅበር ሕጋዊ አቋሙን ሲለውጥ፡-

1. የንግድ ማኅበሩ ወደ ሌላ የንግድ ማኅበርነት መለወጥ በንግድ ሕጉ መሠረት የሕጋዊ የሰውነት መብቱን እንዲያጣ የማያደርገው ሲሆን የሦስተኛ ወገኖችን ከተለወጠው የንግድ ማኅበር መብታቸውን ወይም ጥቅማቸውን ማስከበር ይችላሉ፤

2. የንግድ ማኅበራት ሕጋዊ አቋማቸውን ሲለውጡ ለውጡን ለመስማማታቸው በሙሉ አባላት የተፈረመ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ ቃለጉባኤ ማቅረብ አለባቸው፤

3. የተለወጠው የንግድ ማኅበር ረቂቅ የመመሥረቻ ጽሑፍ/ መግለጫ ለመዝጋቢው አካል መቅረብ አለበት፤

4. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በተለወጠው የንግድ ማኅበር ስም እና ሕጋዊ አቋም እንዲለውጡ መዝጋቢው አካል ደብዳቤ በመላክ የተለወጠው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ስም እንዲቀርብ

ያደረጋል፣

5. የተለወጠው የንግድ ማኅበር የፀደቀ የመመሥረቻ ጽሑፍ ለመዝጋቢው አካል ማቅረብ አለበት፤

6. የቀድሞው የንግድ ማኅበር የንግድ ምዝገባና የንግድ ሥራ ፈቃዶች ተለውጠው በተለወጠው የንግድ ማኅበር ሕጋዊ አቋም በአዲስ መልክ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

7. ሌሎች የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ድንጋጌዎች ለዚህም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

43. ከግለሰብ ነጋዴነት ወደ ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ስለሚደረግ ለውጥ

1. የግለስብ ነጋዴ ወደ ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሲለወጥ የግብር ክሊራንስ ማቅረብ አለበት፤

2. የግለስብ ነጋዴ ወደ ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሲለወጥ ሰነዶችን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ መግለጫ እና የንብረት ጠባቂ ማቅረብ አለበት፤

3. የግለስብ ነጋዴ ወደ ባለ አንድ አባል ኃላፊነት የተወሰነ የግል ማኅበር ሲለወጥ የተፈጥሮ ስም ያልሆነ ስም መምረጥ አለበት፤

4. መግለጫው በንግድ ማኅበራት የተደነገጉትን የመመሥረቻ ጽሑፍና ቃለጉባኤዎችን የሚተካ ነው፤የመግለጫው ይዘት ቢያንስ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 536 ንዑስ ቁጥር (2) የተቀመጡትን ማሟለት አለበት፤

5. ለኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የተደነገጉ ሌሎች ድንጋጌዎች ለባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበርም ያገለግላል።

ክፍል ስምንት
ስለንግድ ምዝገባና ፈቃድ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

44. በነባር ንግድ ማኅበር ውስጥ አባል ለመሆን የሚገባ የውጭ አገር ዜጋ ወይም የውጭ አገር የንግድ ማኅበር፤

በነባር ንግድ ማኅበር ውስጥ አባል ለመሆን የሚገባ የውጭ አገር ዜጋ ወይም የውጭ አገር የንግድ ማኅበር የሚከተሉትን መረጃዎች ማሟላት አለበት።

1. የተሰማራበት የሥራ መስክ ለውጭ አገር ባለሀብት የተፈቀደ መሆኑ ይጣራል፤

2. የአባልነት ጥያቄው የንግድ ውድድርን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚታይ ከሆነ ከዚህ አካል የተሰጠ የፈቃድ ማረጋገጫ፤

3. በንግድ ማኅበር ውስጥ አባል ለመሆን የሚገባ የውጭ አገር ዜጋ ወይም የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ወደ ነባሩ የንግድ ማኅበር እንዲገባ መስማማቱን የሚገልጽ የነባር ንግድ ማኅበሩ ያልፀደቀ ቃለ ጉባኤ፤

4. ኢንቨስትመንትን በሚያስተዳድሩ ሕጎች ለውጭ አገር ባለሀብት የተደነገገው አነስተኛ ካፒታል ወደ ሀገር ውስጥ ባንክ ያስገባበት ማረጋገጫ፤

5. ወደ ነባሩ የንግድ ማኅበር አክሲዮን ገዝቶ የሚገባው የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ስምምነትን የሚያሳይ ማስረጃ፤

6. የነባሩ ንግድ ማኅበር የጸና የንግድ ሥራ ፈቃድ፤

7. መዝጋቢው አካል መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ቃለ ጉባኤው እንዲጸድቅ የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል፤

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ቃለ ጉባኤ ውሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ጸድቆለመዝጋቢው አካል መቅረብ አለበት።

45. ስለንግድ ወኪል

ማንኛውም የንግድ ወኪል፡-

1. ወካዩ ከሚገኝበት ሀገር ሕጋዊ የሰውነት ማረጋገጫ ያለው መሆኑን እና በሚወክለው የሥራ መስክ ላይ የተሰማራ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ሰነድ ማቅረብ አለበት፣

2. ለተወካዩ በአዋጁ መሠረት የውክልና ሥልጣን የተሰጠበት ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ሰነድ መቅረብ አለበት፤

3. የንግድ ሥራ ፈቃድን ስለመስጠት፣ ስለማደስ፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ለዚህም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

46. ስለኮሚሽን ወኪል

1. ወካዩ ከሚገኝበት ሀገር ሕጋዊ የሰውነት ማረጋገጫ ያለው መሆኑን እና በሚወክለው የሥራ መስክ

ላይ የተሰማራ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ሰነድ ማቅረብ አለበት፣

2. ለተወካዩ የውክልና ሥልጣን የተሰጠበት ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ሰነድ መቅረብ አለበት፤

3. የንግድ ሥራ ፈቃድን ስለመስጠት፣ ስለማደስ፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ እና ስለ ስረዛ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ለዚህም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

47. በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት የድርጅት ስም ወይም የንግድ ስም አፈፃፀም

1. በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሠረት" የንግድ ስም ወይም የድርጅት ስም አንድ አይነት ወይም በሚያሳስት ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ" የሚለው አፈፃፀም ተመሳሳይ መሆን አሳሳች ከመሆን ጋር አብሮ መምጣት ይኖርበታል። "ተመሳሳይ" መሆኑ ብቻ ወይም "አሳሳች" መሆኑ ብቻ እንዳይመዘገብ አይከለክልም፤

2. በመዝጋቢው መስሪያ ቤት ያልተመዘገቡ ሀገር አቀፍ ወይም አለም አቀፍ እውቅና ያላቸው የድርጅት ስሞች ለሌሎች የንግድ ድርጅቶች ተሰጥተው ከተገኙ ይህም በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን የንግድ ድርጅት ስሙን እንዲቀየር ስሙን እየተጠቀመበት ላለው ነጋዴ በአንድ ወር (ሠላሳ ቀናት) ጊዜ ውስጥ እንዲያስተካክል ደብዳቤ ይሰጠዋል። በዚህ ጊዜ ገደብ ካላስተካከለ ስሙ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፤

3. ማንኛውም ነጋዴ በድርጅት ስም ያስመዘገበውን ስም በሌላ እስካልተያዘና መስፈርቶችን እስካሟላ ድረስ በንግድ ስምነት መጠቀም ይችላል፤

4. ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ስምነት የተያዘ ስምን በድርጅት ስምነት እስካልተያዘ ጊዜ ድረስ መስፈርቶቹን አሟልቶ በድርጅት ስምነት መጠቀም ይችላል፤

5. የድርጅት እና የንግድ ስሞችን በማጣራት ሂደት ስሞቹን የሚያጣራው ባለሙያ ውሳኔ ላይ ተገልጋዩ ካልተስማማ ቅሬታውን ለቡድን መሪው በማቅረብ ይወሰናል፤ተገልጋዩ በቡድን መሪው ውሳኔ ካልተስማማ የተቋሙ ውሳኔ የመጨረሻው ይሆናል፤

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ውሳኔ ሰጪ አካላት መቃወሚያቸውን ወዲያውኑ በጽሑፍ ለተገልጋዩ ይሰጣሉ፤

7. የድርጅት ስም ወይም የንግድ ስም አፈፃፀም ዝርዝር ማብራሪያ በአባሪ III ተያይዞ ይገኛል።

48. በጋዜጣ ስለማስነገር

1. በንግድ ሕጉ በጋዜጣ ላይ እንዲነገሩ የተደነገጉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ሚኒስቴሩ ተደራሽ በሆነ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም በዲጂታል ጋዜጣ እንዲወጣ ያደርጋል፤
2. ዲጂታል ጋዜጣ ተደራሽ መሆኑ ሲረጋገጥ በአገልግሎት ጠያቂው ወጪ በጋዜጣ ማስነገሩ ቀሪ ሊደረግ ይችላል።

49. የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስለመስጠት፤

1. የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ አካላት ቴክኖሎጂን በመጠቀም በቀጥታ በበይነ መረብ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አገልግሎት የሚሰጡ አካላት የነጋዴዉን መረጃዎች በሚኒስቴሩ የሚቋቋመው/የተቋቋመው/በማዕከላዊ የመረጃ ቋትን በመጠቀም እና በማጣራት አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
3. የክልል መንግሥታት የንግድ መዝገብ የሚያቋቁሙ ከሆነ የመዘገቧቸውን መረጃዎች ወዲያውኑ ወደ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት እንዲተላለፍ ያደርጋሉ፤
4. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉ ድንጋጌዎች እንደትጠበቁ ሆነው የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ተደራሽ በማይሆኑባቸው ቦታዎች አገልግሎት ጠያቂው በአካል በመቅረብ አገልግሎቶች እንዲሰጡት ይደረጋል፤
5. የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ የአገልግሎት ክፍያዎች በኤሌክትሮኒክ ክፍያ ዘዴዎች መከፈል አለባቸው።

50. የንግድ መዝገብ ለሕዝብ ክፍት ስለመሆኑ

ማንኛውም ሰው በመዝገብ የገባውን መረጃ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ቅጂ ወይም ከመዝገብ የተውጣጣ አጭር ቃል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 87 እና 88 መሠረት መውሰድ ይችላል። ሆኖም ይህንን መረጃ ለማየት ብቻ ከጠየቀ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል አይገደድም።

ክፍል ዘጠኝ
ስለ ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን

51. ኢንስፔክሽን ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተግባራት

1. የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖራቸውና በሕግ እና በአስተዳደራዊ እርምጃ የንግድ ሥራ ፈቃዳቸው ተሰርዞ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ የንግድ ድርጅቶችን የማጣራትና የማረጋገጥ፣
2. የንግድ ሥራ ፈቃድ ኖሮአቸውከተፈቀደላቸው ዓላማ ውጭ የሚሰሩትን የንግድ ድርጅቶችንየማጣራትና የማረጋገጥ፣
3. በንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት ጊዜ ውስጥ የንግድ ሥራ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ የሚሰሩ የንግድ ድርጅቶችን የማጣራትና የማረጋገጥ፣
4. ማንኛውም ነጋዴየንግድ ምዝገባና ፈቃድአገልግሎት ለማግኘት የሚያስፈልጉትን መስፈርት ተሟልቶ አገልግሎት የተሰጠ መሆኑን ከንግድ ደርጅቶች ፋይል ወይም ሰነድ የማጣራትእና የማረጋገጥ፤
5. ማንኛውም የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 26 መሠረት የተጣለበትን ግዴታዎች አሟልቶ መሰራቱን የማጣራትና የማረጋገጥ፣
6. ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሕጎች መሠረት ያገኘውን መብት ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠትን የማጣራትና የማረጋገጥ፤
7. የሚወሰዱ አሰተዳደራዊ እርምጃዎችን ተግባራዊነት የማጣራትና የማረጋገጥ ተግባራት ናቸው።

52. በፍርድ ቤትውሳኔ ወይም በአስተዳደራዊ እርምጃ የንግድ ሥራ ፈቃዳቸው ተሰርዞ ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖራቸው በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩትን ፤ ስለማጣራትና ስለማረጋገጥ

1. በአዋጁ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በንግድ መደብር ውስጥ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ነጋዴ እየሰራ ባለው የሥራ ዘርፍ በዘመኑ የተሰጠ ወይም የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድየ ምስክር ወረቀት ያለው መሆኑን የማጣራትና የማረጋገጥ፤
2. በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) ፣ (ሐ) እና አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ)፣(ሐ) መሠረት በታገደ ወይም በተሰረዘ የንግድ ሥራ ፈቃድ እየተሥራ አለመሆኑን የማጣራትና የማረጋገጥ፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖራቸው ወይም በታገደ እና በተሰረዘ የንግድ ሥራ ፈቃድ የሚሰሩትን ለኢንሰፔክሽን ሥራ በተዘጋጀው አባሪ IV ቅጽ 01 ቼክሊስት መሠረት አስፈላጊውን መረጃ በመሙላትና ተጨማሪ መረጃ በመያዝ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ኢንስፔክተሩ ለቅርብ ሀላፊ ያቀርባል፤
4. በሚቀርበው የኢንስፔክሽን ውጤት መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖራቸው ወይምበተሰረዘ የንግድ ሥራ ፈቃድ የሚሰሩ ነጋዴዎች በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

53. የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው ሆነው ከተፈቀደላቸው የሥራ መደብ ውጭ የሚሰሩትን ስለማጣራትና ስለማረጋገጥ

1. ማንኛውም ነጋዴ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው ሆኖ ነገር ግን እየሥራ ያለው ከተፈቀደለት የንግድ ሥራ መደብውጭ መሆኑን በኢንሰፔክሽን ሥራበማጣራትና በማረጋገጥ በተዘጋጀውአባሪ IV ቅጽ 01 ቼክሊስት መሠረት አስፈላጊውን መረጃ በመሙላት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ከውሳኔ ሃሳብጋር ኢንስፔክተሩ ለቅርብ ኃላፊ ያቀርባል፤
2. በሚቀርበውየኢንስፔክሽን ውጤት መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው ሆኖከተፈቀደለት የንግድ ሥራ መደብ ውጭ የሚሰራ ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አግባብ ያለው ባለሥልጣን አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

54. የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያሳድስ የሚሰራ ነጋዴስለማጣራትና ስለማረጋገጥ፣

1. ማንኛውም ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በበጀት ዓመቱ ባልታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ እየሰራ መሆኑን በማጣራትና በማረጋገጥለኢንሰፔክሽን ሥራ በተዘጋጀውአባሪ IV ቅጽ 01 ቼክሊስትመሠረትአስፈላጊውን መረጃ በመሙላት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ኢንስፔክተሩ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለቅርብ ሀላፊ ያቀርባል፤
2. በሚቀርበውየኢንስፔክሽን ውጤት መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያሳድስ የሚሰራ ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ29 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አግባብ ያለው ባለሥልጣንአስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

55. የንግድ ምዝገባና ፈቃድአገልግሎት ለማግኘት የተቀመጠውን መስፈርት ተሟልቶአገልግሎትየተሰጠ መሆኑንከነጋዴው ፋይል ወይም ሰነድ ስለማጣራትእናስለማረጋገጥ

1. ማንኛውም ነጋዴ በአዋጁ እና በደንቡ መሠረትየንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ለማግኘት የተቀመጡ መሰፈርቶች ተሟልተው አገልግሎት ስለመሰጠቱ በውስጥ ኢንስፔክሽን ሥራ በማጣራትና በማረጋገጥ መስፈርት ሳያሟላ ወይም ሀሰተኛ መረጃ አቅርቦ አገልግሎት ባገኘነጋዴ ላይአስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ መረጃ በማደራጀት የውሳኔ ሃሳብ ለቅርብ ኃላፊው ይቀርባል፤
2. በውስጥ ኢንስፔክሽን ውጤት መሠረት መስፈርት ሳያሟላ ወይም ሀሰተኛ መረጃ አቅርቦ አገልግሎት ያገኘ ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1/መ እና አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 መስረት አግባብ ያለው ባለሥልጣን አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

56. በአዋጁ አንቀጽ 26 መሠረት ነጋዴውግዴታዎችንስለማሟላቱ ማጣራትና ማረጋገጥ

1. ነጋዴው ባስመዘገበው አድራሻ የሚገኝ ስለመሆኑ የማጣራትና የማረጋገጥ፤
2. ነጋዴው የአድራሻ ለውጥ አድርጎ ያስመዘገበ ስለመሆኑ የማጣራትና የማረጋገጥ፤
3. ጅምላ ከጅምላ ወይም ችርቻሮ ከችርቻሮ በተመሳሳይ ደረጃየሚደረግ ግብይት እየተፈፀመ ያለመሆኑን የማጣራትና የማረጋገጥ፤
4. ነጋዴውየንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሲጠይቅ ትክከለኛ መረጃዎችን በማቅረብ ያስመዘገበ ስለመሆኑ የማረጋገጥ፤
5. የንግድ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዋጋ ዝርዝር በግልጽ በሚታይ ቦታ መቀመጡን ወይም በንግድ ዕቃዎች ላይ መለጠፉን የማረጋገጥ፤
6. በተጠቃሚው ሕዝብ ጤንነትና ደህንነት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የተለያዩየንግድ ዕቃዎች በአንድ ስፍራእያካሄደ መሆኑን በውጭ ኢንስፔክሽን ሥራየማጣራትና የማረጋገጥ፤
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 6 መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ ነጋዴበመለየት ለኢንሰፔክሽን ሥራ በተዘጋጀውአባሪ IV ቅጽ 01 ቼክሊስት መሠረት መረጃ በመሙላት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሃሳብይቀርባል፤
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 በውጭ መሠረት የተጣለበትን ግዴታዎች ያልተወጣ ነጋዴ ጉድለቱን እንዲያስተካክል አግባብ ያለው ባለሥልጣን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤይሰጣል፣
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት ነጋዴው ጉድለቱን ያላስተካከለ ከሆነ መረጃ ተደራጅቶ ተጨማሪ አስተዳደራዊና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

57. በአዋጁ መሠረት ነጋዴው የንግድ ሥራ ፈቃዱን ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠቱን ስለማጣራትና ስለማረጋገጥ

1. በውጭ ኢንስፔክሽን ውጤት እናበሚቀርብጥቆማ መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ለሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲነግድበት የሰጠ ወይም ያከራየ እንዲሁምበሕግ እንዲነግዱ ላልተፈቀደላቸውየውጭ አገር ዜጎች የንግድ ሥራ ፈቃድ አሳልፎ የሰጠ ወይም ያከራየ በማጣራት እና በማረጋገጥለኢንሰፔክሽን ሥራበተዘጋጀውአባሪ IV ቅጽ 01 ቼክሊስትመሠረት መረጃ በመሙላትአስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሃሳብለቅርብ ኃላፊ ይቀርባል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃዱን አሳልፎ ለሦስተኛ ወገን ሰጥቶ ከተገኘ

በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) እና አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 4 መስረት አግባብ ያለው ባለሥልጣን አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ እና አስፈላጊ መረጃዎችን በማደራጅት ለሕግ እንዲቀርብ ይደረጋል።

58. የሚወስዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ተግባራዊነት ስለማጣራትና ስለማረጋገጥ

የአዋጁ፣የደንቡና እና የዚህ መመሪያደንጋጌዎች በመጣሳቸው የሚወሰደውን አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ በትክክል ተግባራዊ መሆኑን በውጭ ኢንስፔክሽን የማጣራት እና የማረጋገጥ ሥራ በማከናወንተግባራዊ ባላደረጉት የንግድ ድርጅቶች ላይ በተላለፈውውሳኔ መሠረት አግባብ ያለው ባለሥልጣንአስተዳደራዊእርምጃ በመውሰድ መረጃዎችን በማደራጀት ለሕግ እንዲቀርቡ ይደረጋል።

59. የውጭ ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክተር ሊፈጽመው የሚገባ ተግባርና ግዴታዎች

1. ኢንስፔክተር መሆኑን የሚገልፅ ልዩ መታወቂያ ወረቀት ቁጥጥር ለሚደረግበት የንግድ ድርጅት የማሳየት፣
2. የቁጥጥር ሥራውን በተመለከተ ቁጥጥር ለሚደረግበት የንግድ ድርጅት ስለሚደረገው ቁጥጥር የማስረዳት ፣
3. በቁጥጥር ሥራ የታየውን ጉድለት ለንግድ ድርጅቱባለቤት ወይም ተወካይ ወዲያውኑ የማሳወቅ፣
4. ተቆጣጣሪው ለቁጥጥር ተግባር ሲወጣ የቁጥጥር ተግባራትን ለማስተባበር የተመደበው አግባብ ያለው ኃላፊ ጋር ስለሚቆጣጠረው የንግድ ድርጅት እና ስለሚደረገው ቁጥጥር ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ IV በሆነው ቅጽ 02 መሠረት ስምምነት የማድረግ ፤
5. ተቆጣጣሪው የቁጥጥር ተግባሩን የሚያከናውነው በመንግስት የሥራ ሰዓት ብቻ ሆኖ ነገር ግን አሰፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመንግስት የሥራ ሰዓት ውጪ ቁጥጥር ለማድረግ የንግድ ድርጅቱን ስም የሚግለፅ ልዩ ደብዳቤ ከመስሪያ ቤቱ የመያዝና የማሳየት፤
6. ተቆጣጣሪው ባደረገው የቁጥጥር ተግባር ያገኘውን ውጤት በዚህ መመሪያ አባሪ IV ቅጽ 01 በመሙላት ቁጥጥር ከተደረገበት የንግድ ድርጅት ጋር በመፈራረም ለቅርብ ኃላፊው ከውሳኔ ሀሳብ ጋር የማቅረብ፣
7. በቀረበው የኢንስፔክሽን ውጤት እናአግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚሰጠውውሳኔ መሠረት የተወሰነውን አስተዳደራዊ እርምጃ የመፈጸም፤

8. አንድ የንግድ ድርጅት በተወሰደ የእርምት እርምጃ መሠረት የታየበትን ጉድለት ስለማሰተካከሉ የውጭ ኢንስፔክተሩ በድጋሚ በንግድ ድርጅቱ በመገኘት የማረጋገጥ፤

9. ኢንስፔክተሩየንግድ ድርጅት እሸጋ የሚያከናውን ከሆነ ነጋዴውወይም ንግዱን ለማከናወን የተወከለሰው እና አሰፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጸጥታ አካል ባለበት አስተዳደራዊ እርምጃውን የመፈጸም ግዴታዎች አለበት።

60. ቁጥጥር የሚደረግበት ነጋዴ መብትና ግዴታ

1. ነጋዴው የተቆጣጣሪውን ማንነት የሚገልፅ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት የመጠየቅና የማየት፤

2. የቁጥጥር ሥራውን በተመለከተ ማንኛውንም መረጃ የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው፣

3. ለኢንስፔክሽን ሥራ የንግድ ሥራ ቦታውን በሥራ ሰዓት የመክፈት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥራ ስዓት ውጭ ክፍት የማድረግ፤

4. የንግድ ሥራ ፈቃድ እና ሌሎች ከንግድ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ግዴታ የገባባቸውን መረጃዎች ይዞ የመገኘት ግዴታ አለበት።

61. የአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ ስርዓት

1. ኢንስፔክተሩ በኢንስፔክሽን የተገኙ ጉድለቶችን በመረጃና በሪፖርት በማጠናቀር ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለቅርብ ሀላፊ ያቀርባል፤

2. አግባብ ያለው ባለሥልጣን በቀረበውየኢንስፔክሽን ውጤት እና የውሳኔ ሀሳብ ላይ በመመስረት እና በመረጃ በማስደገፍ ከአዋጁና ደንቡ ጋር አገናዝቦውሳኔ ይሰጣል፤

ክፍል ዐሥር
የማጠቃለያ ድንጋጌዎች

62. የመተባበር ግዴታ

1. የውጭ ድኅረ-ፈቃድ ተቆጣጣሪ አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን ማንኛውንም ዓይነት መረጃዎች ፎቶ ኮፒ በማድረግ፣ ፎቶ ግራፍ በማንሳት ወይም መረጃዎችን በመረጠው መንገድ ለመውሰድ እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፣

2. ይህን መመሪያ ለማስፈፀም ሁሉም አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፤

3. ይህን መመሪያ በማስፈፀም ሂደት በተለየ ሁኔታ የፀጥታ አካላት የመተባባር ግዴታ አለባቸው።

63. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

በዚህ መመሪያ ከተደነገጉ ጉዳዮች ጋር ተቃራኒ የሚሆን ማንኛውም መመሪያ አሰራር ወይም ተለምዶ ተፈፃሚነት አይኖረውም፣

64. የተሻሩ መመሪያዎች

የንግድ ስምን ስለማጣራት የወጣው መመሪያ ቁጥር 003/2007 እና የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና የድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 010/2009 በዚህ መመሪያ ተሸሯል።

65. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 01 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ገብረመስቀል ጫላ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር

አባሪ I

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መጠየቂያ የማመልከቻ ቅጾች

የአገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ

1/ የጠየቁት አገልግሎት ዓይነት [“√” ምልክት በማድረግ ይግለፁ]

☐ንግድ ድርጅት ስም/የንግድ ስም ማጣሪያ

☐ኒዲስ ንግድ ምዝገባ

☐ኒዲስ ንግድ ስራ ፈቃድ

☐ ማሻሻያ /ምዝገባ/ ንግድ ፈቃድ፣ ድርጅት ስም/ንግድ ስም

☐ የንግድ ፈቃድ ዕድሳት

☐ ስረዛ /ምዝገባ/ ንግድ ፈቃድ፣ ድርጅት ስም/ንግድ ስም

☐ ምትክ /ምዝገባ/ ንግድ ፈቃድ፣ ድርጅት ስም/ንግድ ስም

ሌላ ከሆነ ይግለፁ _____

2/ አመልካች

2.1/ ግለሰብ ነጋዴ

ሀ. ሙሉ ስም ..... መ. ዕድሜ.....

ለ. የእናት ስም ..... ሠ. ዜግነት.....

ሐ. ጾታ ሴ ወ☐ ረ. ☐ር ከፋይ መለያ ቁጥር.....

2.2/ የንግድ ማህበር

ሀ. የማህበሩ የንግድ ስም _____

ለ. የስራ አስኪያጅ ሙሉ ስም _____

ሐ. ሕጋዊ አቋም

የኅብረት ሸርክና ማኅበር ሁለት ዓይነት☐ ላፊነት ያለበት የሸርክና ማኅበር ☐

ኃላፊነቱ የተወሰነ የሸርክና ማኅበር አክስዮን☐ ኅበር ☐

ኃላ/የተ/የግ/ማ ባለአንድ አባ☐ላ/የተ/የግ/ማ ☐

2.3/ በውጭ አገር የተቋቋመ የግለሰብ ማህበር

ሀ. የተቋቋመበት አገር _____

ለ. የንግድ ስራው ዓይነት/ዋና ዘርፍ _____

3/ የንግድ ሥራ አድራሻ

ሀ. ክልል _____ ከተማ/ዞን _____ ወረዳ/ቀበሌ _____

ለ. ከተማ _____ ክፍለ ከተማ_____ ወረዳ/የቤ/ቁ _____

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ The Federal Democratic Republic of Ethiopia
የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር Ministry of Trade and Regional Integration

ሐ. የቢሮ ስልክ _____ ሞባይል _____

መ. ፋክስ _____ ኢ-ሜይል _____

ሠ. ፓ.ሣ.ቁ _____

4/ ለንግድ ስራው የተመዘገበው ካፒታል

ሀ. የተፈረመ/የፀደቀ ብር _____

ለ. የተከፈለ ብር _____

ሐ. ጠቅላላ የአክሲዮን ብዛት _____

መ. የአንድ አክስዮን ዋጋ ብር_____

5 / የጠየቁት የአገልግሎት ዓይነት

5.1/ አዲስ የንግድ ምዝገባ ማሻሻያ የአድራሻ ለውጥ /ምትክ/ ስረዛ /የጠፋ/ የተበላሸ ከሆነ፣

ሀ. በባለ ፈቃዱ/ በግለሰቡ/የንግድ ማህበሩ ስም ላይ ለውጥ ካለ በተ/ቁጥር (2.1) ወይም (2.2) ወይም (2.3) የተዘጋጀ ባዶ ቦታ ላይ ይሙሉ

ለ. የተለወጠ አድራሻ (ካለ)

ክልል _____ ከተማ/ዞን _____ ወረዳ/ቀበሌ _____

ከተማ _____ ክፍለ ከተማ _____ ወረዳ የቤ/ቁ _____

የቢሮ ስልክ _____ ሞባይል _____

ሌላ ከሆነ ይግለፁ _____

ሐ. የተሰረዘው/የተሰረዙት የንግድ ስራ ፈቃድ ቁጥር/ቁጥሮች _____

መ. የሚመለሰው ምዝገባ ቁጥር _____

5.2 የንግድ ስም ማጣሪያ የምስክር ወረቀት ማግኘት ከሆነ

ሀ. የባለፍቃዱን /የግለሰቡ/ የንግድ ማህበሩን ሙሉ ስም ማጣራት ቢያስፈልግዎ ስሙን በተ/ቁ (2.1) ወይም(2.2) ወይም (2.3) ከተገለፀው ባዶ ቦታ ላይ ይሙሉ

ለ. በተ/ቁ (3) ስር በተገለፀው ባዶ ቦታ ላይ አድራሻውን ይሙሉ

ሐ. እንዲጣራ የጠየቁትን የድርጅት/የንግድ ስም በቅድም ተከተል ስሙን በአማርኛና እንግሊዘኛ ይፃፉ

1. በአማርኛ -- _____

በእንግሊዝኛ -- _____

2. በአማርኛ -- _____

በእንግሊዝኛ-- _____

3. በአማርኛ-- _____

በእንግሊዝኛ-- _____

6/ ማረጋገጫ

11115፣11311፣35411፣36811፣36911፣39141፣51114፣51213፣61511፣61711፣62314፣62714፣63119፣64111፣65412፣65221፣65615፣65753፣65811፣66131፣66212፣66217፣66331፣72131፣84112፣84116፣85121፣85211፣85212፣86116፣86316፣86318፣86411፣86511፣86513፣91113፣91411፣92127፣92131፣93111፣93123፣93211፡-

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Regional Integration

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Trade and Regional Integration

በዚህ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጫ መደብ ያለብቃት አረጋጋጭ መስሪ ቤት ምስክር ወረቀት መስራት የማይቻል መሆኑን። (This License is invalid without respective competency certificate) ተገንዝቤ ፈቃዱን ካወጣሁ በኋላ ብቃት አረጋጋጭ መ/ቤት በመሔድ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የምወስድ መሆኔን እና በዚህ ማመልከቻ ቅጽ ውስጥ የተገለጹት፣ የተሞሉትና በአባሪነት አያይዤ ያቀረብኳቸው ማስረጃዎች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

የአመልካቹ ሙሉ ስም ----------

ፊርማ ----------

ቀን ----------

<u>ማሳሰቢያ</u>

ሀ. ይህን ቅጽ ከሞሉ በኋላ ማቅረብ ስለሚጠበቅብዎት ማስረጃ የአባሪውን ዝርዝር ይመልከቱ፤

ለ. የንግድ ደርጅት በ6 ወር ጊዜ ውስጥ በን/ኢ/ሚ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ላይ ካልተመዘገበ እንደተመዘገበ አይቆጠርም፤

ሐ. የተሻሻለው የንግድ ስም/ድርጅት ስም እስከ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ፀድቆ ለሚመዘገበው አካል ቀርቦ ካልተመዘገበ እንደተሻሻለ አይቆጠርም።

1.አባሪ

ሀ. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሰርተፊኬት ኮፒ
ለ. የአመልካች የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ /የሚሰራ ፓስፖርት/የመንጃ ፈቃድ/የመሥሪያ ቤት መታወቂያ/ፎቶኮፒ.....
ሐ. አመልካቹ 6 ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተነሳው 4 ፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶ ግራፍ
መ. ምትክ ጥያቄ ከሆነ የንግድ ምዝገባ፣ የንግድ ፈቃድ የተበላሸ ከሆነ የተበላሸውን መመለስ
ሠ. የጠፋ ከሆነ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ
ረ. የተጠየቀው የንግድ ስራ መስክ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ማቅረብ
ሰ. ለንግድ ፈቃድ ዕድሳት የግብር ክሊራንስ ማቅረብ
ሸ. ማሻሻያ ከሆነ የተሰጠውን የንግድምዝገባዋና ሠርተፊኬት፣የንግድ ፈቃድ ዋና ሠርተፊኬት

አመልካቹ የንግድ ማህበር ከሆነ ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ

ሀ. የፀደቀ መመሥረቻ ጹሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ፣
ለ. አክሲዮን ማህበር ከሆነ ተፈርሞ የፀደቀ ካፒታል አንድ አራተኛ (1/4) በባንክ ዝግ ሂሳብ ተቀማጭ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ፣
ሐ. የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም ማናቸውም የንግድ ዓላማ ያለው በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ሌላ ተቋም ከሆነ የተቋቋመበትን አዋጅ ወይም ደንብ እንዲሁም የሥራ አስኪያጁን የሹመት ደብዳቤ ማቅረብ፣
መ. የውጭ ሀገር ዜጋ /ማህበር ከሆነ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና የግለሰቡ የታደሰ ፓስፖርት እና ገፆች ፎቶ ኮፒ ማቅረብ አለበት።

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ The Federal Democratic Republic of Ethiopia
የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር Ministry of Trade and Regional Integration

ሠ. ማሻሻያ ከሆነ የተሰጠውን የንግድ ምዝገባ ዋና ሠርተፊኬት፣የንግድ ፈቃድ ዋና ሠርተፊኬት እና ማሻሻያ የሚደረግባቸውን ማስረጃዎች /በህግ አካል የፀደቀ ዋና ቅጂ ቃለ ጉባኤ/

ለመ/ቤቱ አገልግልት ብቻ

ከላይ የቀረበው ማመልከቻ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ 980/2008 እናበማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1150/2012 /መሠረት ትክክለኛ እና መረጃዎች የተሟሉ ስለሆነ ብር ---------- ከፍለው አገልግልት እንዲያገኙ አድርጌያለሁ።

ያረጋገጠው ባለሙያ ሙሉ ስም ----------

ፊርማ ----------

ቀን ----------

አባሪ II

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት የምስክር ወረቀቶች

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF TRADE AND INDUSTRY

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/TIN Tin
የንግድ ምዝገባ ቁጥር RegNo
Principal Registration No
የቀድሞው የምዝገባ ቁጥር PrivousRegNumber
Previous Registration No
የቀድሞው የምዝገባ ቀን PrivousDateRegistered
First Registration Date RegDate
መጀመሪያ የተመዘገበበት ቀን
xrLabel105

የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት
በንግድ ምዝገባና የፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 መሰረት የተሰጠ

Commercial Registration Certificate
Issued under Commercial Registration and Business license proc No. 980/2016

1.የግለሰቡ/ድርጅቱ ስም
BusinessNameAmh

2. ዜግነት NatAmh

3. የሥራ አስኪያጅ ስም
ManagerNameAmh

4. የንግድ ድርጅቱ አድራሻ

ክልል amDescription ዞን/ክፍለ ከተማ WADesc
ወረዳ xrLabel11 ቀበሌ KADesc
የቤት ቁጥር HouseNo ስልክ ቁጥር Tel
ፋክስ Fax ኢ-ሜል Email

5. ካፒታል በኢት. ብር Capital

6. የተሰማራባችው የንግድ ሥራዎች
Division

1.Owner/ Company Name
BusinessName

2. Nationality NatEng

3. General Manager Name
ManagerNameEng

4. Business Address

Region description Zone/Sub City WDesc
Woreda xrLabel50 Kebele KDesc
House No. HouseNo Tel. No Tel
Fax Fax E-mail Email

5. Capital in ETB Capital

6. Type of activities engaged
EngDivision

በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር Tin የተመዘገበ መሆኑን እናረጋግጣለን ::
ይህ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ዛሬ RegDate ዓ.ም
በ አዲስ አበባ ተሰጠ =

has duly been registered under TIN Tin
This Registration Certification is issued in
on Addis Ababa RegDate

የኦፊሴል ስም/Official's Name ፊርማ/Signature
ማህተም/Seal

ማሳሰቢያ:- 1 ይህ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በማስያዣና ወይም በእዳ ሊያዝ አይችልም።
N.B. The holder of this License is forbidden for surety ship or debt

This application was created using the trial version of the XtraReports.

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ኢንዱስቲ ሚኒስቴር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF TRADE AND INDUSTRY

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Trade

የግብር ከፋይ መለያ ዊ. /TIN	TIN
የንግድ ምዝገባ ቁ. Principal Registration No.	RegNo
የቀድሞው ንግድ ፈቃድ ቁጥር Previous License No.	PrivouslicenceNumber
የንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር Business License No.	LicenceNumber
ቀድሞ ተሰጠበት ቀን Previous Date of issuance	PrivousDateRegistered
የተሰጠበት ቀን Date of issuance	EventDateTime

የንግድ ሥራ ፈቃድ

በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 መሰረት ተሰጠ

1. የግለሰቡ/ድርጅቱ ስም — AmFullName
2. ዜግነት — NationalityAmh
3. የንግድ ስም — TradeNameAmh
4. ሥራ አስክያጅ ስም — ManagerNameAmh
5. የንግድ ድርጅቱ አድራሻ
   - ክልል — RADesc
   - ዞን/ክፍለ ከተማ
   - ወረዳ
   - ቀበሌ — KADesc
   - የቤት ቁጥር — HouseNo
   - ስልክ ቁጥር — Tel
   - ፋክስ — Fax
   - ኢ-ሜይል — Email
6. የንግድ ሥራ መስክ — AmSubGroup
7. ካፒታል በኢት ብር — Capital

ይህ የንግድ ፈቃድ ዛሬ በ አዲስ አበባ ተሰጠ ።

የሃላፊ ስም/Name of Official _____

ፊርማ/Signature _____

ማህተም
Seal

Business License

Issued Under Commercial Registration and Business license proc.No 980/2016

1. Owner/Company Name — EngFullName
2. Nationality — NationalityEng
3. Trade Name — TradeNameEng
4. General Manager Name — ManagerNameEng
5. Business Address
   - Region — REDesc
   - Zone/Sub City
   - Woreda — WEDesc
   - Kebele — KEDesc
   - House No. — HouseNo
   - Tel.No — Tel
   - Fax — Fax
   - E-mail — Email
6. Field of Business — EngSubGroup
7. Capital in ETB — Capital

This Business License is issued in this day — Addis Ababa

ለ_____ታድሷል

ማሳሰቢያ- N.B.

1. ይህ የንግድ ፍቃድ በዓዋጅ ፈቃድ ቁጥር 980/2008 መሠረት እንደ የበጀት ዓመቴ በአዋጅ በተቀመጠው መሰረት መታደስ አለበት።
This License Shall be renewed in accordance with Proclamation No. 980/2008 as per the fiscal year.

2. ይህ የንግድ ፈቃድ የምስክር ወረቀት በዋስትና ወይም በእደ ሊያዝ አይችልም።
The holder of this License is forbidden for surety ship or debt.

This document is created using the trial version of the XtraReports.



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የንግድ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Trade

የመንግስ ቀጥሪ ሥራኒ ቁጥር
የንግድ ኮዱን ማህደ ቁ. ጥበቃ
የንግድ ምዝገባ ቁ.
Principal Registration No.
የምርት ስም ምዝገባ ቁጥር
Trade Name Reg.No.
የንግድ ሥራ ፈቃዱ ሠየር
Business Licence No.

Tin
RegNo
RegNo
LicenceNumber

የንግድ ስም ምስክር ወረቀት

በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 መሰረት የተሰጠ

Trade Name Registration Certificate

Issued under Commercial Registration and Bussiness licence proc.No 980/2016

1. የባለቤት/የድርጅት ስም
AhmName

2. የንግድ ስራ መስክ
MajorDivision

3. የንግድ ድርጅቱ አድራሻ
ክልል AmRegion ዞን AmZone
ክፍለ ከተማ AmWoreda ወረዳ AmKebele
የቤት ቁጥር HouseNo ስልክ ቁጥር Tel
ፋክስ Fax ኢ-ሜይል Email

4. የንግድ ስም
TradeNameAmh

ይህ የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት ዛሬ _____
ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ የተሰጠ

1. Manager / Business Name
EngName

2. Field of Bussiness
MajorEngDivision

3. Business address
Region EngRegion Zone EngZone
Sub city EngWoreda Wereda EngKebele
House No. HouseNo Tel.No. Tel
Fax Fax E-Mail Email

4. Trade Name
TradesName

This Trade Registration Ceritificate is issued in
Addis Ababa this day _____

ማህተም
Seal

የሀላፊ ስም _____
Official's name

ፊርማ _____
Signature

ማሳሰቢያ፡- ይህ የንግድ ስም የምዝገባ የምስክር ወረቀት በማስተላለፍ ወይም በሌላ ሊያዝ አይችልም።
The holder of this Licence is forbidenfor survey skip or debt

This application was created using the trial version of the XtraReports.

አባሪ III

የድርጅት እና የንግድ ስም ማብራሪያ

የድርጅት እና የንግድ ስም ምዝገባ ማብራሪያ

የድርጅት እና የንግድ ስም ምዝገባ የሚከናወነው በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 16 መሠረት ነው፡፡ በአዋጁ መሠረት ማንኛውም በንግድ ሥራ ሊሰማራ የሚፈልግ ሰው በንግድ መዝገብ በሚመዘገቡበት ቦታ የንግድ ስሙን ማስመዝገብ ይኖርበታል፡፡

የድርጅት እና የንግድ ስም ዓላማ

የድርጅትና የንግድ ሥም ምዝገባን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ዓላማ በሦስት መልኩ የሚታይ ነው፡፡

- አንደኛው እንዲመዘገብ የተጠየቀው ሥም ቀደም ብለው ከተመዘገቡ የንግድ ሥሞች ጋር አንድ ዓይነት ወይም በሚያሳስት ደረጃ ተመሳሳይ እንዳይሆን ማድረግ ነው፡፡
- ሁለተኛው ደግሞ ሕብረተሰቡ በንግድ ስሙ አማካኝነት ስለንግዱ የተሳሳተ መረጃ እንዳይወስድ ማድረግ ነው፡፡
- ሦስተኛው ዓላማ ደግሞ የንግድ ስሙ ከሞራል ወይም ሥነ- ምግባር ተቃራኒ እንዳይሆን መቆጣጠርነው፡፡

እነዚህ ሦስት ዓላማዎች በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጁ የንግድ ሥም ድንጋጌዎች ላይ በተለያየ መልኩ ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ የንግድ ስምን የሚመለከቱት የአዋጁ ዋና ዋና ድንጋጌዎችን ከዚህ በታች ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

1.በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ስም ቀደም ብሎ ከተመዘገቡት የንግድ ሥሞች ጋር አንድዓይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች መሆን የለበትም፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ለምዝገባ የቀረበው ሥም ቀደም ብለው ከተመዘገቡ የንግድ ስሞች ጋርአንድዓይነት ወይምተመሳሳይና አሳሳች ሊሆን አይገባም፡፡

ሀ. ቀደምብለው ከተመዘገቡ ሥሞች ጋር አንድ ዓይነት ያልሆነ፤

አንድ ነጋዴ ቀደም ብሎ ከተያዘ የንግድ ሥም ጋር አንድ ዓይነት ስም ማስመዘገብ አይችልም፡፡ ምክንያቱም፡-

- ስሙ የንግዱን ዓይነት በግልፅ የማይለይ በመሆኑና ይህም በተለያዩ የንግድ አይነቶች ማንነት ላይ መደናገርን ስለሚፈጥር ፤
- ሕብረተሰቡ ስሙ የትኛውን ንግድ እንደሚያመለክት ለማወቅ ሊቸገር ስለሚችል፤

- ንግዱ በአስፈፃሚ አካላት በቀላሉ የሚለይበት ስም ሊኖረው ስለሚገባ ነው።

የቀረበው የንግድ ሥም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለመሆኑ ብዙ አስቸጋሪ ሆኖ አይታይም። እንዲመዘገብ የተጠየቀው ሥም በንግድ ሥም መዝገቦች ላይ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ብቻ የሚጠይቅ ነው።

ይህንን ድንጋጌ በተመለከተ ሁለት ጉዳዮች ግልፅ ሊሆኑ ይገባል።

- አንደኛው ምዝገባውን ለመከልከል አዲሱ ሥም በማንኛውም ሁኔታ ቀደም ብሎ ከተመዘገበው ስም ጋር አንድዓይነት(identical) መሆን ይኖርበታል። ማለትም በሁለቱ ስሞች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት ሊኖር አይገባም።

- ሁለተኛው ጉዳይ ቀደም ብሎ የተመዘገበው ስም በሥራ ላይ ያለ ወይም በተለያዩ ምክንየቶች ያልተሰረዘ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል።

የነጋዴው የንግድ ምዝገባ ሲሰረዝ የተመዘገበው የንግድ ስም መሰረዝ ይኖርበታል። ይህም ማለት አንድ የንግድ ስም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ሥም ጋር አንድዓይነት መሆኑን ለመወሰን የምንመለከተው ሥራ ላይ ያሉ ነጋዴዎችን የንግድ ስሞች ብቻ ነው።

በተለያዩ ምክንያቶች ከተሰረዙ የንግድ ሥራ ፈቃዶች ጋር የተያያዙ የንግድ ሥሞችን መመልከት አይኖርብንም።

ለ. ቀደም ብለው ከተመዘገቡ ስሞች ጋር ተመሳሳይና አሳሳች ያልሆነ

እንዲመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ስም ቀደም ብሎ ተመዝግቦ በሥራ ላይ ካለ ሌላ የንግድ ስም ጋር ሙሉ በሙሉ አንድ ዓይት ባይሆንም “ተመሳሳይና አሳሳች” ሊሆን ይችላል። አዲሱ የንግድ ስም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ሌላ የንግድ ሥም ጋር ተመሳሳይና አሳሳች ሆኖ ከተገኘ በንግድ ሥምነት ሊመዘገብ አይችልም።

ወደ ዝርዝር ከመገባቱ በፊት መታወቅ ያለበት ጉዳይ በዚህ ድንጋጌ የተከለከለው ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር “ተመሳሳይ” ብቻ ሳይሆን “አሳሳችም” መሆን ይኖርበታል። ይህም ማለት እንዲመዘገብ የቀረበው የንግድ ሥም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር “ተመሳሳይ” በመሆኑ ብቻ ምዝገባ አይከለከልም። “ተመሳሳይ” ቢሆንም “አሳሳች” ላይሆን ይችላልና።

አንድ የንግድ ሥም ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር “ተመሳሳይና አሳሳች” (confusingly similar) የሚሆነው መቼነው? የሚለው ጥያቄ በንግድ ምዝገባ ሥርዓቱ ወሳኝ የሆነ ነገር ግን ቁርጥ ያለ መልስ ሊሰጥበት የማይችል ጉዳይ ነው። ጉዳዩ መወሰን የሚኖርበት የሚቀርቡትን ሥሞች በማወዳደር፣ በመመርመርና በማገናዘብ በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ እንደሁኔታው (on a case -by- case- basis) ነው።

በአጠቃላይ ግን አንድ የንግድ ሥም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር “ተመሳሳይና አሳሳች” ነው የሚባለው ሁለቱ ሥሞች ከመቀራረባቸው የተነሳ ሕብረተሰቡ አንዱን ሥም ከሌላው ጋር በማምታታት ሊሳሳት ይችላል ተብሎ ሲታመን ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ስም ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር “ተመሳሳይ እና አሳሳች” መሆኑን ለመወሰን መጀመሪያ “ተመሳሳይ” መሆኑን መወሰን ያስፈልጋል። “ተመሳሳይ” መሆናቸው ከተወሰነ በኋላ ደግሞ “አሳሳች” መሆናቸውም መወሰን ይኖርበታል።

እነዚህን ጉዳዮች ለመወሰን የተለያዩ ማነጻጸሪያዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይቻላል።

ለምሳሌ፦

ሀ/ የሁለቱ ሥሞች ቃላት ቅርርብነት፣

ለ/ የሁለቱ ሥሞች አነባበብ ቅርርብነት፣

ሐ/ የሁለቱ ሥሞች ትርጉም ቅርርብነት እና

መ/ ሁለቱ ሥሞች የሚወክሏቸው የንግድ ዓይነቶች ቅርርብነት ናቸው።

ሀ. በሁለቱ ሥሞች ላይ የሚገኙት ቃላት ቅርርብነት

አንድ ለምዝገባ የቀረበ ሥም ላይ የተጠቀሱት ቃላት ተመዝግቦ በሚገኝ ሌላ የንግድ ስም ላይ ከሚገኙ ቃላት ጋር አንድ ዓይነት ባይሆኑም እጅግ ተቀራራቢ በመሆናቸው አሳሳችሊሆኑ ይችላሉ።

- **ቀድሞ በተመዘገበ ሥም ላይ ቅጽሎችን መጨመር**

ለምሳሌ ፦ ሕብረት ቡና ንግድተብሎ የተመዘገበ የንግድ ስም ቢኖር፤

- የሕብረት ቡና ንግድ
- ሕብረት ቡና ንግድ ቁ. 2
- ሕብረት የቡና ንግድ
- የሕብረት የቡና ንግድ
- ሕ- ብ- ረ-ት ቡና ንግድ
- ሕብ-ረት ቡና ንግድ

- ሕብረቶች ቡና ንግድ ወዘተ ተመሳይና አሳሳች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ።

ነገርግንየአንድ ፊደልለውጥሁለቱን ስሞች ሙሉ በሙሉ ሊለውጥ ይችላል።

ለምሳሌ፦ “ጥረት የድለላ ሥራ” እና “ጥራት የድለላ ሥራ” ሙሉ በሙሉ የተለያዩ ስሞች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ተመዝግቦ በሚገኝ ሥም ላይ ሌላ ሙሉ ቃል ቢጨመርበት ተመሳሳይና አሳሳች ሊባል አይችልም።

ለምሳሌ፦እድገት በኅብረት ቡና ንግድ

ሕብረት ለሥራ ቡና ንግድ

ሕብረት ለእድገት ቡና ንግድ ወዘተ የሚሉ የንግድ ስሞች **“ሕብረት ቡና ንግድ”** ተብሎ ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ንግድ ስም ጋር “ተመሳሳይና አሳሳች” ናቸው ማለት አይቻልም።

- **የቃላትን ቅደም ተከተል መቀያየር**

አንዳንድ ጊዜ ቀደም ብሎ የተመዘገበ ሥም ላይ የሚገኙ ቃላትን ቅደም ተከተል በመለዋወጥ የሚቀርብ የንግድ ስም ምዝገባ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ አዲሱ የንግድ ሥም ቀደም ሲል የተመዘገበውን የንግድ ሥም ቃላት በምን ያህል ደረጃ ቅደም ተከተላቸውን በመቀያየር አሳሳች እንዳይሆን አድርጓል የሚለው መታየት ይኖርበታል።

ለምሳሌ፦“ሕብረት የቡናና ሻይ ንግድ“ የሚል ቀደም ብሎ የተመዘገበ የንግድ ሥም ቢኖር እና "ሕብረት የሻይና ቡና ንግድ” የሚል የንግድ ስም ለምዝገባ ቢቀርብ የተደረገው የቃላት ቅደም ተከተል መጠናኛና በአጠቃላይ በንግድ ስሙ ላይ ጎልቶ የወጣ ልዩነት የማያመጣ በመሆኑ “ተመሳሳይና አሳሳች” ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ የተደረገው የቃላት ቅደም ተከተል ለውጥ ከፍተኛ በመሆኑ በሁለቱ የንግድ ሥሞች መካከል የሚኖረው ልዩነት በግልፅ የሚታይ ሊሆን በሚችልበት ጊዜ አዲሱ የንግድ ስም ቀድሞ ከነበረው የንግድ ስም ጋር ተመሳሳይና አሳሳች አይደለም ተብሎ ሊመዘገብ ይችላል።

ለምሳሌ፦ሲስተም ኤሌክትሮኒክስ ንግድ እናኤሌክትሮኒክስ ሲስተም ንግድተመሳሳይና አሳሳች ላይባሉ ይችላሉ።

የግለሰብ ስም የንግድ ስም ሆኖ መመዝገብ

የግለሰብ ስሞች የንግድ ስም ሆነው ሊመዘገቡ ይችላሉ። ይሁንና ተመሳሳይ የግል ስሞች በመኖራቸው አንድ ነጋዴ ስሙን በንግድ ስምነት ካስመዘገበው ሌላ ነጋዴ የራሱ ስም ቢሆንም በንግድ ስምነት ለመጠቀም ቀድሞ ከተመዘገበ የንግድ ስም ጋር አንድ ዓይነት ነው ተብሎ ሊከለከል ይችላል።ይህ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ

በተቻለ መጠን ከተመዘገበው የንግድ ሥም ሊለይ የሚችለበትን ጭማሪ በማድረግ ለመመዝገብ መሞከር ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፡ “ወንድወሰን - የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ” የሚል የተመዘገበ የንግድ ስምቢኖር ስሙ ወንድወሰን የሆነ ሌላ ነጋዴ ተመሳሳይ ስም ለተመሳሳይ የንግድ ሥራ ሊያስመዘግብ አይችልም። ይሁንና በስሙ ላይ ተጨማሪ ስም ወይም ቃል በመጨመር ሊመዘገብ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል።

ለምሳሌ፡-

- ወንድወሰን ቶላ ጉርሜ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ
- ወንድወሰን ቶላ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ
- ወንድወሰን 8798 የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድወዘተ የሚሉት የንግድ ስሞች ሊመዘገቡ ይችላሉ።

እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን ማስታወስ ያስፈልጋል። አንደኛ አንድ አይነት የግለሰብ ስሞች ለተለያዩ የንግድ ሥራዎች የንግድ ስም ሆነው ሊመዘገቡ ይችላሉ ምክንያቱም በዚህ ጊዜ አሳሳች ሊሆኑ ስለማይችሉ ነው።

ለምሳሌ፡ “ወንድወሰን የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ” የሚለው የንግድ ስም ቢኖርም “ወንድወሰን ፍራፍሬ ንግድ”፣ “ወንድወሰን ጨርቃጨርቅ ንግድ” ወዘተ የሚሉ የንግድስሞች ሊመዘገቡ ይችላሉ።

ሁለተኛው ፆታን ገላጭ ስሞች አንድዓይነት ስሞች ወይም “ተመሳሳይና አሳሳች” ላይሆኑ ይችላሉ፡

ለምሳሌ፡-

- ታደለ እና ታደለች
- ዘነበ እና ዘነበች
- አበበ እና አበበች
- ተሾመ እና ተሾመች ወዘተ ሁል ጊዜ አንድ ዓይነት ወይም “ተመሳሳይና አሳሳች” ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም።

ለ. የሁለቱ ሥሞች አነባበብ ቅርርብነት

አንዳንድ ጊዜ ሊመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ሥም አፃፃፍ ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር ልዩነት ቢኖረውም በአነባብ ግን “ተመሳሳይና አሳሳች” ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል።

ለምሳሌ፡-

- ኩልል የመጠጥ ውሃ እናኩል የመጠጥ ውሃ
- Kool water እናCool water
- Koka –kola እናCoka – kola
- መጋቢት 15 ልብስ ስፌት እናመጋቢት አሥራ አምስት ልብስ ስፌትተመሳሳይና አሳሳች ስሞች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ።

ሐ. የሁለቱ ሥሞች ትርጉም ቅርርብነት

ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ሥም ቃላቶቹ ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር የተለያየ ቢሆንም ትርጉማቸው ግን አንድ አይነት ወይም የተቀራረበ ሊሆን ይችላል።

ለምሳሌ፡-

- አስተማማኝ ኮንስትራክሽን እናሪላይብል ኮንስትራክሽን
- ሎያል ትራንዚት እናታማኝ ትራንዚት

የእነዚህ ስሞች ትርጉሞቻቸው አንድ ዓይነት ወይም ተቀራራቢ ቢሆኑም በራሳቸው ሲታዩግን ፈፅሞ የተለያዩ ናቸው። ኅብረተሰቡም ሁለቱን ስሞች ያምታታቸዋል ተብሎ አይገመትም። በመሆኑም እነዚህ ስሞች ሁል ጊዜ አሳሳች ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም።

መ. ሁለቱ የንግድ ሥሞች የሚወክሏቸው የንግድ ዓይነቶች ቅርርብነት

ሁለት የንግድ ስሞች ተመሳሳይና አሳሳች ሊሆኑ የሚችሉት የሚወክሏቸው የንግድ ዓይነቶች አንድ ዓይነት ወይም በጣም የተቀራረቡ ሲሆኑ ነው። ይህም ማለት አንድ ዓይነት የንግድ ስም ለተለያዩ የንግድ ዓይነቶች ሊሰጥ ይችላል።

ለምሳሌ፡- “ሞሐ የለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ” የሚል የንግድ ሥም ቢኖርም፤

- “ሞሐ የወፍጮ ንግድ ሥራ”
- “ሞሐ የልብስ ስፌት ሥራ”
- “ሞሐ ባልትና” ወዘተ የንግድ ስሞችን መመዝገብ ይችላሉ።

በተመሣሣይ “አማኑኤል ፈለቀ ካፌ” የሚል የንግድ ሥም ቢኖርም፤

- “አማኑኤል ፈለቀ የእንጨት ሥራ”
- “አማኑኤል ፈለቀ ፋርማሲ”
- “አማኑኤል ፈለቀ የድለላ ሥራ” ወዘተ የሚሉ የንግድ ሥሞች ሊመዘገቡ ይችላሉ።

<u>ማጠቃለያ</u>

አንድ የንግድ ሥም ቀድሞ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር “ተመሳሳይና አሳሳች” መሆን አለመሆኑ ሁለቱን ሥሞች ከላይ በተገለፁትና በሌሎች መመዘኛዎች በማወዳደር የሚወሰን ጉዳይ ነው። በተግባር የተለያዩ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ያሉትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት መወሰን ይኖርባቸዋል።

በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ)የንግድ ስሙ ቀደም ሲል ያልተመዘገበ ቢሆንም ሌሎች ነጋዴዎችን ወይም ኅብረተሰቡን የሚያሳስት አለመሆኑ

እንዲመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ስም ቀደም ብሎ ያልተመዘገበ ቢሆንም ሕብረተሰቡን ሊያሳስት የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል። ሊያሳስት ይችላል ተብሎ ከታመነም በንግድ ሥምነት አይመዘገብም።

ሕብረተሰቡን ሊያሳስትባቸው ከሚችልበት ሁኔታዎች የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

1. በአዋጁ አንቀጽ 16ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ)እንዲመዝገብ የተጠየቀው ስም ንግዱ ያላግባብ ከመንግስትጋር ግንኙነት እንዳለው ሊያስመስል ከቻለ ላይመዘገብ ይችላል። መንግስት የራሱን አስተዳደራዊ ተቋማት የሚሰይምበት ስሞች አሉ።

ለምሳሌ፦

- ኮሚሽን
- ኤጀንሲ
- መምሪያ
- ቢሮ

- ማዘጋጃ ቤት ወዘተ...

እነዚህ ስሞችን በንግድ ስምነት መጠቀም ኅብረተሰቡ ንግዱ ከመንግስት ጋርግንኙነት አለው ብሎ እንዲያስብ ሊያደርገው ይችላል።

ለምሳሌ፦

- ሠላም የማዳበሪያ አስመጭ ኮሚሽን
- ታታሪ የሠራተኛና አሠሪ አገናኝ ቢሮወዘተ አሳሳች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ።

አንድ የንግድ ስም ከመመዝገቡ በፊት ከመንግስት አካላት ወይም ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ስሞች ጋር የማይመሳሰል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ለምዝገባ የተጠየቀው ስም ከመንግስት አካላት ወይም ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ስሞች ጋር ተመሳሳይ ከሆነ የምዝገባው ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም።

ይሁንና ለዚህ ድንጋጌ አፈፃፀም ሁለት ጉዳዮችን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በመጀመሪያ ደረጃ መዝጋቢው ስሙ ከየትኛው የመንግስት አካል ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ስም ጋር እንደሚመሳሰል ማሳየት አለበት። የመንግስት አካላት የሚጠሩበት ሥሞች ተለይተው ታውቀው ለምዝገባ የቀረበው ሥም ከእነዚህ ሥሞች ጋር ያሳስታል ተብሎ መወሰን ይኖርበታል። በኢትዮጵያ የመንግስት አካላት ሥሞች በተለያየ ጊዜ ሊለዋወጡ ይችላሉ። በአሁኑ ጊዜ የሚታወቁት ሥሞች የሚከተሉትን ያካትታል፤

- ሚኒስቴር
- ኮሚሽን
- ኤጀንሲ
- ቦርድ
- ድርጅት
- የክልል መስተዳደር
- የክልል ቢሮ
- የዞን መስተዳደር

- የከተማ መስተዳድር
- ማዘጋጃ ቤትወዘተ…

የመንግሥትየልማትድርጅቶችን ሥም በተመለከተ እያንዳንዱ የልማት ድርጅት የሚቋቋመው በሕግ እንደመሆኑ የልማት ድርጅቶችን ሥም ማወቅ የሚቻለው ከሚቋቋሙበት ሕግ ላይ ነው።

ሁለተኛው ጉዳይ የተጠየቀውን የንግድ ስም ምዝገባ ለመከልከል ስሙ ከመንግስት አካላት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ስም ጋር አንድ ዓይነት መሆን አይጠበቅበትም። ይልቁንም ለምዝገባ የተጠየቀው ስም ከመንግስት አካላት ስም ወይም ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ስም ጋር ተመሳሳይ ከሆነ አይመዘገብም። የዚህም ምክንያት ሕብረተሰቡ በስሞቹ ሊሳሳት ስለሚችል ነው። በመሆኑም ለምዝገባ የቀረበው ስም ከመንግስት አካላት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ስም ጋር አንድ ዓይነት ካልሆነ ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ መወሰን አለበት።

አንድ የንግድ ስም ከመመዝገቡ በፊት ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የሠራተኛ ማኅበር ወይም ሌላ አይነት ማኅበር ወይም የእርዳታ ድርጅት ስም ጋር ተመሳሳይ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

የዚህ ድንጋጌ ዓላማ ከአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) ጋር ተመሳሳይ ነው። ይኸውም ለመመዝገብ የቀረበው ስም ከፖለቲካ ፓርቲ ወይም ከሠራተኛ ማኅበራት ወይም ከዕርዳታ ድርጅቶች ሥሞች ጋር ተመሳሳይ ከሆነ ሕብረተሰቡ የንግድ ድርጅቱ ከፓርቲዎች ወይም ከሠራተኛ ማኅበራት ወይም ከዕርዳታ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት አለው ብለው እንዲያስቡ በማድረግ ሊያሳስቱት ይችላሉ የሚልነው። መዝጋቢው ይህንን ውሳኔ ለመወሰን የሚመለከተው ሥም ኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ስሞች ወይም ተመዝግበው የሚታወቁ የሠራተኛ ማኅበራትን ስሞች ወይም የዕርዳታ ድርጅቶችን ስሞች ነው።

ለምሳሌ፡- “ፋኦ (FAO) የወተት ልማት ንግድ” የሚል የንግድ ሥም ለምዝገባ ቢቀርብ ፋኦ (Food and Agricultural Organization) ከሚባለው ተቋም ስም ጋር ተመሳሳይ ነው ሊባል ይችላል።

በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) የታዋቂ ስዎችን ስሞች በንግድ ስምነት መጠቀም

የታዋቂ ስዎችን ስሞች በንግድ ስምነት መጠቀም የሚገድብባቸው ሁለትዋነኛ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። አንደኛው ኅብረተሰቡ እንዳይሳሳት ለማድረግና ሁለተኛው ደግሞ የታዋቂ ስዎችን ክብር ለመጠበቅ ሲባል ነው።

አንድ ነጋዴ የታዋቂ ሰዎችን ስም በንግድ ስምነት በመጠቀም እነዚህ ሰዎች በኅብረተሰቡ ዘንድ ያላቸውን መልካም ዝና ያላግባብ ለመውሰድ ሊሞክር ይችላል። ኅብረተሰቡ የታዋቂ ሰዎችን ሥም የተጠቀመውንግድ ከታዋቂው ሰው ጋር ግንኙነት ይኖረዋል የሚል እምነት ሊያድርበት ይችላል።

ለምሳሌ፦ ሀይሌ ገብረስላሴ በሩጫው ዓለም እውቅናን ያተረፈ ሰው ነው። እንዲሁም ሀይሌ በተለያዩ የንግድ ሥራዎች ላይ መሰማራቱ ይታወቃል።ኅብረተሰቡ ሀይሌን በሩጫ ብቻ ሳይሆን በንግድም ያውቀዋል። አንድ ነጋዴ "ሀይሌ ገብረሥላሴ ብረታብረት ንግድ" የሚል የንግድ ሥም ቢጠቀም ኅብረተሰቡ ንግዱን ከሀይሌ ገብረ ስላሴ ጋር ሊያገናኘው ይችላል። በመሆኑም የንግድ ስሙን ለማስመዝገብ የኃይሌን ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

የታዋቂ ሰዎች ሥሞች በንግድ ስምነት መጠቀም የሚገደብበት ሌላው ምክንያት ደግሞ የታዋቂውን ሰው ክብር ለመጠበቅ ነው። አንድ ነጋዴ የታዋቂ ሰዎችን ወይም የሀገር መሪዎችን ስም በንግድ ስምነት መጠቀም የሚችለው ተገቢውን ፈቃድ ሲያገኝ ብቻነው። ይህ ድንጋጌ የሚያካትታቸው "የታዋቂ ሰዎቸን" እና "የሀገርመሪዎችን" ሥሞች ነው። ይሁንና "ታዋቂ ሰዎች" የሚለው የሀገር መሪዎችንም ያካትታል ምክንያቱም የሀገር መሪዎች በሕብረተሰቡ ዘንድ ታዋቂ ስለሚሆኑ ነው።

ለዚህ ድንጋጌ ተፈፃመሚነት መመለስ የሚጋባቸው ጥያቄዎች ይኖራሉ። የመጀመሪያው ጥያቄ ታዋቂ ሰዎች ወይም የሀገር መሪዎች እነማን ናቸው? የሚለው ነው። የሀገር መሪዎችን ስም በኢንተርኔትና መሰል ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ማወቅ ብዙም ላያስቸግር ይችላል። የታዋቂ ሰዎችን ዝርዝር ግን ማግኘቱ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ውሳኔው እንደሁኔታው እየታየ የሚሰጥነው። ሰዎች ከሌሎች በተለየ መልኩ ታዋቂ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል። በፖለቲካ፣ በስፖርት፣ በሥነ-ጽሑፍ፣ በሙዚቃ ወዘተ ሰዎች በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ታዋቂነትን ሊያገኙ ይችላሉ። እዚህ ላይ ሊታወቅ የሚገባው ጉዳይ ግን ስሙ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታወቅ ሰው ስም መሆን ይኖርበታል። በሌላ አገላለፅ ሰውየው በአማካኝ ኢትዮጵያዊ የሚታወቅ መሆን ይኖርበታል። ኔልሰን ማንዴላ፣ ባራክ ኦባማ፣ አበበ ቢቂላ፣ ጥላሁን ገሠሠ፣ ማይክል ጃክሰን፣ ወዘተ አማካኝ ንቃተ ሕሊና ላለው ኢትጵያዊ የሚታወቁ ሥዎች ናቸው። ታዋቂነቱም በሀገር ዐቀፍ ደረጃ መሆን ይኖርበታል።

ድንጋጌው በየአካባቢው የሚታወቁ ሰዎችን የሚያካትት ከሆነ ለአፈፃፀም እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል። በመሆኑም መካተት የሚኖርባቸው በብሔራዊ ደረጃ ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን ሥሞች መሆን ይኖርበታል። ለምሳሌ ቀነኒሳ በቀለ በብሔራዊ ደረጃ የሚታወቅ ሰው ነው። በአንድ ወረዳ ወይም ቀበሌ የሚታወቅን ሰው ሥም ድንጋጌው ማካተት የለበትም። በዚህ መሠረት እንደ ሁኔታው የሚለዩ ታዋቂ ሰዎች ሥምን ለንግድ ሥምነት ለመጠቀም "ተገቢ ፈቃድ" መገኘት ይኖርበታል። ይህም ማለት ታዋቂው ሰው ሥሙ በንግድ ሥምነት እንዲያገለግል ግልፅ የሆነ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል። አመልካቹ የታዋቂ ሰው ሥም በንግድ ሥምነት ለመጠቀም ፈቃድ ማግኘቱን ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል። ሌላው መነሳት ያለበት ጥያቄ ድንጋጌው በህይወት የሌሉ ታዋቂ ሰዎችን ወይም የሀገር መሪዎች ሥምን ያካትታል ወይስ በሕይወት ላሉት ብቻ የተወሰነነው? የሚለው ነው። በአንዳንድ ሀገሮች ታዋቂ ሰዎች በህይወት የሌሉ ከሆነ ከወራሾቻቸው ፈቃድ እንዲሰጥ ይጠየቃል። ታዋቂ ሰዎች ወራሾች የሌሉ ከሆነ ግን ሥሙን ያለ ፈቃድ ለመጠቀም ይቻላል።በዚህ ጉዳይ ላይ ግልፅ የሆነ ድንጋጌ አልተቀመጠም።

በመሆኑም ድንጋጌው የሚያገለግለው በህይወት ለሚኖሩ ታዋቂ ሰዎች ስም ነው ብሎ መደምደም ይቻላል።

የሚመዘገበው ስም በኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ ሥምነት ያልተመዘገበ ቢሆንም በሌሎች አገራት የሚታወቅ ወይም ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ካላቸው ስሞች መካከል መሆን የለበትም

ይህ ድንጋጌ የሚመለከተው ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገቡ የተወሰኑ የንግድ ስሞችን ነው። ሁለት ዓይነት ሥሞችን የሚመለከት ነው። አንደኛው በሌሎች አገራት የሚታወቅ ስም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያለው ሥም ነው።

በሌሎች ሀገራት ልምድ እንደሚታየው በአንድ ሀገር ሕግ መሠረት ያልተመዘገበ የንግድ ሥም ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂነት ያላቸው የንግድ ሥሞች ጥበቃ የሚደረግላቸው በሀገሮች መካከል በሚደረግ ሥምምነት መሠረት ነው። የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጁ ግን ስምምነት ቢኖርም ባይኖርም በሌሎች ሀገራት የሚታወቁናዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን የንግድ ስሞች ጥበቃ ያደርግላቸዋል።

በሌሎች ሀገራት ታዋቂ የሆኑ ስሞች ይኖራሉ። ይሁንና እነዚህን ሥሞች ለማወቅ ቀላል ላይሆን ይችላል። ለምሳሌም አንድ የንግድ ስም በሩዋንዳ የታወቀ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህንን ስም ኢትዮጵያ ውስጥ ለማወቅ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ለዚህ ስም ኢትዮጵያ ውስጥ ጥበቃ የሚደረግበት ምክንያት ግልፅ አይደለም። በመሆኑም በኢትዮጵያ ያልተመዘገበ ነገር ግን በሌሎች ሀገራት ታዋቂ የሆነ የንግድ ስም ጥበቃ የሚደረግለት በኢትዮጵያ የሚታወቅ ሲሆን ብቻነው። በኢትዮጵያ የማይታወቅ ከሆነ የማይመዘገብበት ምክንያት የለም። በኢትዮጵያ የሚታወቅ ሲባል ግን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያውቀው ይገባል ማለት አይደለም። የንግድ ሥሙ በሚታወቅበት የንግድ ዓይነት ወይም ሴክተር ኢትዮጵያ ውስጥ መታወቅ ይኖርበታል። ለምሳሌ አክሰስ ባንክ በናይጀሪያ የታወቀ ስም ሲሆን በኢትዮጵያ የባንክ ሴክተርም የታወቀ ስም በመሆኑ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ የሚሸፍን ይሆናል።

በአለም ዓቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ የንግድ ስሞችም አሉ። ኮካ- ኮላ፣ አፕል፣ ሶኒ፣ ማይክሮ ሶፍት፣ ስታርባክስ፣ ሒልተን ፣ ቶዮታ ወዘተ በሰፊው ከሚታወቁ የንግድ ስሞች ጥቂቶች ናቸው። እነዚህ ስሞች ኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ ስምነት ባይመዘገቡም በኢትዮጵያውያን ዘንድ በስፋት የሚታወቁ ስሞች ናቸው። እነዚህን ሥሞች ኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ ስምነት ማስመዝገብ የሚቻለው ስሙን ለማስመዝገብና ለመጠቀም ፈቃድ መሰጠቱን የሚያሳይ ማረጋገጫ ሲቀርብነው። የሚቀርበው ማረጋገጫ የተለየ ፎርማት ባይኖረውም በጽሑፍ መሆን ይኖርበታል።

- የአመልካቹ መጠሪያ ስም ወካይ ሲሆን ወይም
- ከንግድ ማኅበራት አባላት ስም የተውጣጣ ከሆነ የአባላቱን ስሞች የመጀመሪያ ፊደላት ብቻ የያዘ

ሲሆን ነው።

አንዳንድ ምህፃረ ቃላት ትርጉም ያላቸው ሲሆን ሌሎች ደግሞ ትርጉም የማይሰጡ ይሆናሉ። በአዋጁ መሠረት ለንግድ ስምነት የቀረቡት ምህፃረ ቃላት ትርጉም ያላቸው ከሆነ ሊመዘገቡ ይችላሉ።

ለምሳሌ፡-ጉ.ተ ኢንተርኔት ካፌ (ጉና ተራራ)

- አ.ም ሎጅ (አርባ ምንጭ)
- ኪ.ም የአሸከርካሪዎች ማሰልጠኛ (ኪዳነ ምህረት)
- መ.ፎ የመንፅር ሥራ (መልቲ ፎካል)
- መ.ታ ኮንስልተንሲ (መልቲ - ታለንት)

በተመሳሳይ መልኩ ለንግድ ስምነት የቀረበው ምህፃረ ቃል የአመልካቹ ስም ወካይ ከሆነም ሊመዘገብ ይችላል።

ለምሳሌ፡

- ሸምሱ ሁሴን የሚባል ነጋዴ ሸ.ሁ ፍራፍሬ ንግድ" የሚል የንግድ ስም ሊኖረው ይችላል።
- ከበደ ማሞ ቶላ የሚባል ነጋዴ "ከ.ማ.ቶ የመኪና ኪራይ" የሚል የንግድ ስም ሊኖረው ይችላል።

ከንግድ ማኅበራት አባላት ሥም የተውጣጣ ከሆነ ደግሞ የአባላቱን ስሞች የመጀመሪያ ፊደላት ብቻ የያዘ ሲሆን ምህጻረ ቃሉ በንግድ ስምነት ሊመዘገብ ይችላል።

ለምሳሌ በላይ፣ ኪሮስ፣ ስንቅነሽ እና ሌንጮ የሚባሉ ሰዎች አንድ የንግድ ማኅበር ቢያቋቁሙ በ.ኪ.ስ.ሌ የሚል የንግድ ስም ሊያስመዘግቡ ይችላሉ።

ይህንን ድንጋጌ በተመለከተ ሁለት ነገሮች ግልፅ ሊሆኑ ይገባል። አንደኛው ድንጋጌው የሚመለከተው ምህፃረ ቃል ብቻ በንግድ ሥምነት ሲቀርብ ነው። ምህጻረ ቃሉ ከሌላ ቃላት ጋር ተጨምሮ ለንግድ ስምነት ሊቀርብ ይችላል። ለምሳሌ "ጉ.ማ.ኔ አዋሽ ቆዳ ሥራ" የሚል የንግድ ስም ለምዝገባ ቢቀርብ ጉ.ማ.ኔ የሚለውምህፃረ ቃል ትርጉም ቢኖረውም ባይኖረውም ወይም የባለቤቱን ስም ይወክል አይወክል ሊመዘገብ ይችላል።

ሁለተኛው ጉዳይ ምህፃረ ቃሉ ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ስም ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች ከሆነ ወይም ለሞራል ተቃራኒ ከሆነ ወዘተበተዘረዘሩ ሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት ላይመዘገብ ይችላል። ለምሳሌ ባምላኩ፣ ለማ እና ጌታሁን የተባሉ ሰዎች የስሞቻቸውን የመጀመሪያ ፊደል በመውሰድ "ባ.ለ.ጌ"

የሚል የንግድ ስም ማስመዝገብ ቢፈልጉ ሥሙ ከመልካም ጠባይ ወይም ሥነ - ምግባር ተቃራኒ ነው ተብሎ ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል።

በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ረ) የንግድ ስም ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን የለባቸውም

ለምዝገባ የቀረበ የንግድ ስም በተለያዩ ምክንያቶች ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ - ምግባር ተቃራኒ ሊሆን ይችላል። አንድ ስም ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን አለመሆኑ እንደ የሀገራቱ ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያዩ ይችላል። አንድ ማኅበረሰብ ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሚላቸው በሌላ ማኅበረሰብ በተመሳሳይ ላይታዩ ይችላሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን በተለያዩ ሁኔታዎች ሊመጣ ይችላል።

ለምሳሌ፡

- አንድን ሀይማኖት የሚያንቋሸሽ ሥም፣
- አንድን ቋንቋ ብሔር /ብሔረሰብ የሚያንቋሸሽ ስም፣
- ስካርን፣ ሴሰኝነትን፣ አደንዛዥዕፅን፣ ወንጀልን የሚያበረታታ ስም
- የአንድን ሰው መልካም ዝና የሚያጎድፍ ስም
- የአንድ ፆታ የበታችነት የሚያመለክት ስም፣
- ጦርነትን፣ ብጥብጥን የሚያበረታታ
- ጥላቻን የሚያመላክት
- የሀገራትን መልካም ስም የሚጎዳ ስም ወዘተ...

አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ረ)አንድ ስም ለመልካም ጠባይ ወይም ሰነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን አለመሆን በእያንዳንዱ ሁኔታ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። በአሁኑ ዘመን ግልፅ በሆነ መልኩ ለመልካም ጠባይ ወይም ለስነ-ምግባር ተቃራኒ የሆኑ የንግድ ስሞች በጣም ውስን ሊሆኑ ቢችሉም ሙሉ በሙሉ የሉም ማለት ግን አይቻልም። ይህ በሚያጋጥምበት ወቅት እንደ አጠቃቀሙ ሁኔታ (context) መወሰን ይኖርበታል።

ለምሳሌ፡- “ፍለርት ባር” (Flirt Bar) የሚለው የንግድ ስም ለምዝገባ ቢቀርብ ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ-ምግባር ተቃራኒ መሆን አለመሆኑ አጠያያቂ ሊሆን ይችላል። የእንግሊዘኛው ቃል “Flirt” መቀራረብን፣

መፈላለግን፣ መነካካትን ወዘተ የሚያሳይ ነው። ቃሉን በቡና ቤት ደረጃ ስንመለከተው ፆታዊ መቀራረብ፣ መተሻሸት ወዘተ የሚደረግበት ቦታን ሊያመለክት በመቻሉ ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

አባሪ IV

የድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መረጃ ማሰባሰቢያ ቼክ ሊስትና ቅጽ

	የኢፌዲሪንግድሚኒስቴር	ቅጽ01	
የውጭ ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ ሥራ ቼክ ሊስት ቅጽ		የተሰጠው ቁ.	

1.የንግድ ድርጅቱ/ነጋዴው/ ስምና አድራሻ

1.1.የድርጅቱ/የነጋዴው/ ስም_____

1.2.የድርጅቱ ባለቤት/ኃላፊ/ ዜግነት_____

1.3. አድራሻ፡-

ክልል_____ከተማ___ ክ/ከ_____ወረዳ___ የቤ.ቁ_____የስልክ ቁጥር_____

2. የድርጅቱ/ግለሰቡ/ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሁኔታ

2.1.የንግድ ፈቃድ ቁጥር _____

2.2.የግብር መክፈያ መለያ ቁጥር(ቲን ቁጥር)_____

2.3. የንድ ሥራ ዘርፍ _____

2.4. የንግድ ሥራ መስክ_____

3. የድርጅቱ/ግለሰቡ ቦታ ይዞታ ባለቤት/የውል ማስረጃ

ሀ) አለው ለ) የለውም

4. ድርጅቱ/ግለሰቡ እየሰራ ያለው ባስመዘገበው አድራሻ

ሀ) ነው ለ) አይደለም

5. የንግድ ሥራ ፍቃድ እድሳት ሁኔታ

ሀ) ታድሷል ለ) አልታደሰም

5.1. የንግድ ፈቃዱ የታደሰበት ጊዜ_____

6. ከተፈቀደለት ፈቃድ ውጪ የሚሸጠው/የሚሰጠው አገልግሎት

ሀ) አለ ለ) የለም

7. የድርጅቱ/ግለሰቡ የመረጃ አያያዝ ሁኔታ

7.1 የሚሸጣቸው ዕቃዎች ከየት እንደተገዙ የሚገልፅ ደረሰኝ

ሀ) አለ ለ) የለም

7.2. የሚሸጣቸው የዕቃዎች ዓይነት እና የዋጋ ዝርዝር ለተገልጋይ በሚታይ መልኩ

ሀ) ተለጥፏል ለ) አልተለጠፈም

7.3.የሚሸጣቸው ዕቃዎች እና አገልግለቶች ሕጋዊ ደረሰኝ

ሀ) ይሰጣል ለ) አይሰጥም

8. አጠቃላይ በሥራ ላይ የታዩ ጉዳዮች

_____

_____

_____

_____

9. የኢንስፔክተሩ አስተያየት

_____

_____

_____

_____

10. ኢንስፔክሽን የተካሄደበት ቀን _____ ሰዓት _____

11.የኢንስፔክሽን ሥራውን ያካሄደው ኢንስፔክተር ስምና ፊርማ

ስም ፊርማ

1. _____ _____
2. _____ _____
3. _____ _____
4. _____ _____

12. ኢንስፔክሽን በተካሄደበት ወቅት የነበረው የንግድ ድርጅት ባለቤት/ኃላፊ/ተወካይ/ሠራተኛ

ስም ፊርማ ቀን

1. _____ _____ _____

ማውጫ

ክፍል አንድ 1

ጠቅላላ ድንጋጌ 1

ክፍል ሁለት 2

የድርጅት ስም እና የንግድ ስም ስለመመዝገብ፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ 2

ክፍል ሦስት 6

የንግድ ምዝገባ ስለ መመዝገብ ስለ ማሻሻል፣ ስለ ምትክ እና ስለስረዛ 6

ክፍል ዐራት 10

የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት፣ ስለማደስ፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ 10

ክፍል አምስት 14

በልዩ ምዝገባ ስለመመዝገብ፣ ስለዕድሳት፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ 14

ክፍል ስድስት 19

የንግድ መደብርን ስለማስተላለፍ፣ ስለንግድ ማኅበራት መዋሃድና መከፈል 19

ክፍል ሰባት 21

ስለንግድ ማኅበራት ሕጋዊ አቋም ለውጥ 21

ክፍል ስምንት 22

ስለንግድ ምዝገባና ፈቃድ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 22

ክፍል ዘጠኝ 25

ስለ ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን 25

ክፍል ዐሥር 31

የማጠቃለያ ድንጋጌዎች 31

አባሪዎች 33

አባሪ I 33

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መጠየቂያ የማመልከቻ ቅጾች 33

አባሪ II 38

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት የምስክር ወረቀቶች 38

አባሪ III 42

የድርጅት እና የንግድ ስም ማብራሪያ 42

አባሪ IV 58

የድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መረጃ ማሰባሰቢያ ቼክ ሊስትና ቅጽ 58